# የሸሪዓ ሕግ ዓላማዎች (መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ)

አልዩ አባተ ይማም*


**አህጽሮተ-ፅሁፍ**

*የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት አንዱና ዋነኛ መገለጫው፣ በሕግ እውቅና ያገኘ የሕግ ብዝኃነት የሥርዓቱ አካል መደረጉ ነው። በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 35(4) እና 78(5) መሠረት፣ ከመንግሥት የፍትሕ ሥርዓት በተጓዳኝ መደበኛ ያልሆኑ፣ ባህላዊና የሃይማኖት የዳኝነት ተቋማት ተቋቁመው፣ የግልና የቤተሰብ ጉዳዮች፣ በተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ በባህላዊ ወይም በሃይማኖታዊ ሕጎች ሊዳኙ እንደሚችሉ ይደነግጋል። ይህን ሕገ-መንግስታዊ የብዝኃነት እውቅና በተጨባጭ እውን ያደረጉት ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ብቻ ናቸው። ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ከዘውዳዊዉ የኃይለ-ሥላሴ ዘመነ-መንግሥት በፊት ጀምሮ ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ በሃገሪቱ የፍትሕ ሥርዓት ዉስጥ ሲሰሩ የነበሩ ሲሆን፣ ይህ እዉነታም በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት እውቅና ተሰጥቶት፣ በፌዴራልና በክልል ደረጃ በሦስት የዳኝነት እርከኖች ተቋቁመው በመስራት ላይ ይገኛሉ። የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 3 መሠረት፣ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች የኢስላም ሕግን ተፈጻሚ በማድረግ የሚዳኙ መሆኑ ተደንግጓል። ይህ ጽሁፍ፣ ከሸሪዓ መሠረተ-ሐሳቦች መካከል አንዱና ዋነኛው የሆነውን የሸሪዓ ዓላማዎችና ግቦች (መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ) የሚዳስስ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በእለት ተዕለት የዳኝነት ሥራቸው ውስጥ፣ የሸሪዓ የግል፣ የቤተሰብና የውርስ ሕጎችን ሲተረጉሙና ተፈጻሚ ሲያደርጉ፣ የጠቅላላውን የሸሪዓ ሕግ ዓላማዎች እና የየዘርፉን ንዑስ ዓላማዎችን በሚያሳካ አኳኋን መሆን ይችል ዘንድ የመስኩን ሥነ-ጽሁፍ ዋና ዋና እና መንደርደሪያ ፍሬ-ሐሳቦች ያብራራል። የቃል በቃል የሕግ አተረጓጎም ተግባራዊ በማድረግ፣ በቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮች፣ መዝሓቦችና (የሕግ ትምህርት ቤቶች)፣ እና ሊቃውንት (ሙጅተሒዱን፣ ፉቅሓእ) ከዳበረው ዝርዝር የሸሪዓ የሕግ ማዕቀፍ ጀርባ፣ በ20ኛው ክፍለ-ዘመን የሸሪዓ ምሁራን ጥልቅ ጥናት እየተደረገበት ያለውንና፣ ሸሪዓን ከዘመኑ የማሕበረሰብ ሥልጣኔ እና እዉነታዎች ጋር ለማጣጣም አይነተኛ መሳሪያ የሆነውን የመቃሲድ እድገት፣ ዘዴዎች፣ መርሆዎችን መረዳትና መተግበር እጅግ አስፈላጊ ነው። የሸሪዓ ሕጎች በጠቅላላው አንድ የታወቀ የፍትሕ (ዐድል)፣ ጥቅምን የማረጋገጥ (መሷሊህ) ወይም መልካም ግለሰባዊ ሰብዕናን የማነጽ (ተሕዚብ አል-ፈርድ) እና ማሕበረሰባዊ የግብረ-ገብ እሴቶችን የማስጠበቅ ዓላማዎችን ያነገቡ ናቸው። ከዚሁ ጥቅል የሸሪዓ ዓላማ በታች፣ የቤተሰብና የውርስ ሕግን ጨምሮ፣ ሁሉም የሸሪዓ ዐብይ እና ንዑስ ዘርፎች የየራሳቸው ዓላማዎች አሏቸው። ትክክለኛ የሸሪዓ ሕግ ግንዛቤ እና የፍትሕ ሥርዓት ለመዘርጋት፣ በጥንታዊው የቃል በቃል፣ ደረቅ የሕግ አተረጓጎም ምትክ፣ ዓላማና መንፈስ ላይ ያነጣጠረ የሕግ አረዳድ ባህል ሊዳብር ይገባል። የሸሪዓ ሕግ፣ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት በተሰጠው የተፋጻሚነት ወሰን ውስጥ በመሆን እየተሰራበት መሆኑን መሠረት በማድረግ፣ የሸሪዓ የፍትሕ ሥርዓቱ የሕግ አውጪውን ዓላማ ማሳካት እና ተለማጭ መሆን ይችል ዘንድ፣ በመቃሲድ ላይ ሐሳቦችን ማንሸራሸር አስፈላጊ ነው፤ ስለሆነም በዚህ ጽሁፍ በመቃሲድ አጭር ታሪካዊ አነሳስና እድገት፣ መቃሲድ የሚለይባቸው ዘዴዎችና መርሆዎች እና ሌሎች ተዛማጅ መሠረታዊ ርዕሶች ተዳሰዋል።*


**ቁልፍ ቃላት፡-** *መቃሲድ፣* የሸሪዓ ዓላማዎች፣ ጥቅል የሕግ ዓላማዎች፣ *ኢጅቲሓድ፣* ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር።

## መግቢያ፡- የርዕሰ-ጉዳዩ አግባብነትና ጠቀሜታ

የሸሪዓ ሕግ ዓላማዎችን *(መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ)* በመስኩ ሥነ-ጽሁፍ የተተነተነውን ያህል ባይሆን እንኳ፣ የመቃሲድን ምንነት፣ ንድፈ-ሐሳቦችን፣ የምርምር ዘዴዎችንና እና አጠቃላይ መሠረታዊ ፍሬ-ሐሳቦቹን የሚዳስስ፣ ጽሁፍ ለኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ያለው አግባብነትና ጠቀሜታ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ በአንባቢው በኩል ሊነሳ ይችላል፡፡ የዚህ ምላሽ ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ማቋቋሚያ ሠነድ ከሆነው የፌዴራል ሕገ-መንግሥት አንቀጾች የሚገኝ ነው፡፡[1] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 34(5) እና 78 (5) ላይ እንደተደነገገው፣ ከኦፌሴላዊ የመንግሥት የሕግና ፍትሕ ሥርዓት በተጓዳኝ እውቅና ሊሰጣቸው የሚችሉ የሕግ ሥርዓቶች አሉ፤ እነሱም ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ሕጎች ናቸው፡፡ በሕብረተሰቡ ውስጥ ለሚነሱ ግላዊና የቤተሰብ ግጭቶች፣ በባለጉዳዮቹ ፈቃድ በባህል ወይም በሃይማኖት ሕጎች መሠረት ሊዳኙ እና እልባት ሊሰጣቸው እንደሚችል ሕገ-መንግሥቱ ያትታል፡፡

ተቋማዊ አደረጃጀቱን በተመለከተ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78(4) ላይ እንደተመለከተው፣ የግልና የቤተሰብ ግጭቶችን የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው ሃይማኖታዊና ባህላዊ ፍርድ ቤቶችን የማቋቋም ሥልጣን ለፌዴሬሽኑ የሕግ አውጪ አካላት፣ ማለትም በፌዴራል ደረጃ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በክልሎች ደረጃ ደግሞ ለክልል ምክር-ቤቶች ተሰጥቷል፡፡ በዚህ የሕገ-መንግሥት ድንጋጌ መሠረት፣ የባህል እና የሃይማኖት ፍርድ-ቤቶችን የማቋቋም ጥያቄዎችን ተቀብሎና ገምግሞ፣ በቂ ፍላጎት ያለና አስፈላጊነቱ የታመነበት ከሆነ፣ በሕግ አውጪዎቹ ይሁንታ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ፍርድ ቤቶች ተቋቁመው የሕግ ብዛኃነቱ አካልና ተዋናይ እንዲሆኑ ሊደረግ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ እንደ እድል ሆኖ፣ ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጪ ያሉ የዳኝነት አካላት የሚቋቋሙበት ይህ ሥርዓት፣ ለሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተፈጻሚ አይሆንም፤ እንዴት ከተባለ ምላሹ በአንቀጹ ንዑስ 5 ላይ ይገኛል፡፡ ይኸውም፣ ሕገ-መንግሥቱ ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ የባህል ወይም የሃይማኖት ፍርድ ቤቶች እውቅና አግኝተው እንዲደራጁ የሚያስገድድ በመሆኑ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ታሪክ ደግሞ፣ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከአጼ ኃይለ-ሥላሴ ሥርዓተ-መንግሥት በፊት ጀምሮ በሥራ ላይ የነበሩ በመሆኑ፣[2] በንጉሱ ዘመን ደግሞ የቃዲና የናኢባ ፍርድ ቤቶች ተብለው በ1934 እና በ1936 ዓ.ል በወጡ የማቋቋሚያና የማሻሻያ አዋጆች ተደራጅተው ሲሰሩ የነበሩ ናቸው፡፡[3] ሥለሆነም ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች፣ ከመንግሥታዊ የዳኝነት ተቋማት በተጓዳኝ በመሥራት፣ ከሕገ-መንግሥቱ መጽደቅ በፊት

* (LL.B, ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፣ LL.M, አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በወሎ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ት/ቤት መምህር፡፡ ኢ-ሜይል፡ alyuabate09@gmail.com)

[1] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዲሪ) ሕገ-መንግሥት፣ 1987 ዓም፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ ቁጥር 1

[2] ዛኪ ሙስጠፋ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት የእስላም ፍርድ ቤቶች የሚሰራበት ሕግ፤ ለሸሪዓ ሕግ በሥራ ላይ መዋል መቀጠል ምክንያት የሆኑ ነገሮች፣ የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት፣ ቅጽ 9፣ ቁጥር 1፣ 1965፣ ገጽ 173 ይመለከቷል፡፡ ጽሁፉ በ፡ http://journals.co.za/docserver/fulltext/jel/9/1/211.pdf?expires=1513428722&id=id&accname=guest&checksum=61C6511681864827D9D37CAE4B9444CE ፌለጉ-ገጽ ላይ ይገኛል (በታህሳስ 12፣ 2010 ዓ.ም የተገኘ)፡፡ See also: Mohammed Abdo, Legal Pluralism, Sharia Courts, And Constitutional Issues In Ethiopia, Mizan Law Review, Vol. 5 No.1, Spring 2011, p. 78. Available at: https://www.ajol.info/index.php/mlr/article/view/68769/56835

[3] የቃዲ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1934 እና የቃዲዎችና የናኢባ ምክር-ቤቶች አዋጅ ቁጥር 62/1936፡፡

ሲሠሩ የነበሩ በመሆኑ፣ እነዚህን ፍርድ ቤቶች በፌዴራልና በክልል ደረጃ አቋቋሞ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ በሕግ አውጪዎች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፣ ሕገ-መንግሥቱ ራሱ ያቋቋማቸው፣ እና እውቅና ማግኘታቸው በሕግ አውጪ አካላት ላይ የተጣለ ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታ መሆኑን ይገነዘቧል።

የፌዴራል ሕገ-መንግሥቱን አስገዳጅ አንቀጽ መሠረት በማድረግ፣ የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም የሚያጠናክሩ እና እንደገና የሚያደራጁ አዋጆችን አውጥተዋል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ‹የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 188/1992› በተሰኘ አዋጅ አማካይነት ፍርድ ቤቶቹ በይበልጥ ተጠናክረውና ተደራጅተው እየሰሩ መሆናቸው የታወቀ ነው። በተመሳሳይ፣ የክልል መንግሥታትም በበኩላቸው፣ የፌዴራል ሕግ መንግሥቱን አንቀጽ 78(5) መሠረት በማድረግ፣ ክልላዊ ተፈጻሚነት ያላቸው የየራሳቸውን የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጆች አውጥተው፣ በሃገሪቱ ዙሪያ በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ፣ የመጀመሪያ፣ ከፍተኛና ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተደራጅተው፣ በተከራካሪዎች ፈቃድ ላይ ተመርኩዘው፣ በግልና በቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ሸሪዓዊ ፍትሕን በማድረስ ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል። ይህም ሕጋዊ እውቅና ያገኘ የሕግ ብዝኃነት *(Legal Pluralism*) የሃገሪቱ የሕግ ሥርዓት አካል እንደሰፈነ የሚያሳይ እውነታ ነው።[4]

በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት፣ ለሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ ጉዳዮች በሸሪዓ ሕግ መሠረት እንደሚዳኙ ይደነግጋል። ለፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ የግልና የቤተሰብ ግጭቶችን ለመዳኘት፣ ተፈጻሚ የሚደረገው የሸሪዓ የግልና የቤተሰብ የሕግ ማዕቀፍ በመተርጎም ረገድ፣ *መቃሲድ* ወሳኝ የመሪነት ሚና የሚጫወት በመሆኑ፣ የርዕሱን ልዩ ልዩ ገጽታዎች መገንዘብ እና በተግባር እንዲንጸባረቅ ማድረግ፣ በየደረጃው ካሉ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እና በሕግ ሙያ ከተሰማሩ ጠበቆችና አማካሪዎች የሚጠበቅ ነው።

የሸሪዓ ሕጎች በሁለት ጥቅል ምድቦች ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ። የመጀመሪያው የአምልኮ ሥነ-ሥርዓት የሚዘረጋው የሸሪዓ ክፍል - *ዒባዳት* ሲሆን፣ ሁለተኛው ምድብ ደግሞ በዓለማዊ ሕይወት ላይ ዘርፈ-ብዙ የግለሰብ እና የማህበረሰብ ግንኙነቶችን የሚገዛው የሸሪዓ ክፍል - *ሙዓመላት* ነው። ሁሉም የሸሪዓ ሕጎች ከሕግነታቸው ጀርባ ሊያሳኳቸው ያለሙት የፍትሕ፣ የግለሰብ እና የማህበረሰብ መብትና ጥቅም የማስከበር ዓላማዎች አላቸው፤ በሌላ አገላለጽ ያለ ዓላማና ግብ *(መቃሲድ)* የተደነገገ የሸሪዓ ሕግ በተለይም የ*ሙዓመላት* ሕግጋት የለም። የ*ዒባዳሕ* ሕጎችም ቢሆኑ፣ ዓላማቸው እውን ሲሆን በተጨባጭ የሚታይ ባይሆንም

---

[4] በሕግ እዉቅና ካገኘ የሕግ ብዝኃነት *(De-jure)* በተቃራኒ፣ ሕግ የማይፈቅደውና እውቅና ያልተሰጠው፣ የፍሬ-ነገር የሕግ-ብዝኃነት *(De-facto)* አለ። ይህ የብዝኃነት ጽንሰ-ሐሳብ፣ በአንድ የሕግ ሥርዓት ውስጥ በተጨባጭ የሚታየውን፣ ከመንግሥታዊ የፍትሕ ሥርዓት በተጓዳኝ የግለሰቦችንና የማሕበረሰብ ባህርይ እና ምግባር የሚቀርጹና የሚመሩ ሕጎች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ነባራዊ እውነታ የሚያመለክት ነው። ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ የሸሪዓ ሕግ ወይም ባህላዊ ሕጎች በባህላዊ እና ሃይማኖታዊ የፍትሕ ተቋማት አማካይነት ከተፈቀዱበት ወሰን አልፈው፣ በፍትሐ-ብሔራዊ፣ በንግድ እና በወንጀል ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ የሚደረጉ መሆኑ የማይካድ ሃቅ ነው። ከሕግ እውቅና ውጪ የሆነው ነባራዊ ብዝኃነት፣ በሃገራዊ የፍትሕ ሥርዓት፣ በጾታ እኩልነት እና የሰብዓዊ መብት፣ በልማታዊ የፖሊሲ አፈጻጸም እርምጃዎች ላይ የራሱ የሆኑ አሉታዊ ሚናዎች ያሉት ሲሆን፣ ለባህላዊና የሃይማኖት የሕግ ሥርዓቶች የተሰጣቸው የእውቅና ደረጃና የተፈጻሚነት ወሰን የተወሰነው፣ ግጭቶችን ለመፍታት ካላቸው ውጤታማነት *(Instrumental Function)*፣ በሰብዓዊ መብቶች፣ በእድገት እና ሥልጣኔ ላይ የሚጋርጧቸው ችግሮች እና ሌሎች ታሳቢዎች ግምት ውስጥ ገብተው መሆኑ ይታወቃል። ከነዚህ እሳቤዎች አንጻር ደጋፊ ወይም ነቃፊ የመከራከሪያ ሐሳቦች ሊቀርቡ የሚችሉ መሆኑ እና እየቀረቡ ያሉ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

የግለሰብን ሰብዕና በማነጽ፣ መንፈሳዊ እርጋታና መልካም ባህርይን በማላበስ፣ ለምድራዊ ሕይወት ስኬት የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡

*መቃሲድ* የሸሪዓ አንድ አካል ነው፤ ስለሆነም ሕጎች ሲተረጎሙ እና ሲተገበሩ የወጡበትን ዓላማ በሚያሳካ አኳኋን መሆን ይኖርበታል፡፡ የሸሪዓ ሕግ ዓላማዎችና ግቦች ወደጎን ተብለው የቃል-በቃል አረዳድ *(Literal Interpretation)* በመከተል ሕጉን ማስፈጸም የሕጉን ዓላማና መንፈስ የማያሳካ ከመሆኑም በላይ ያልታሰበ ጉዳት እና ኢ-ፍትሐዊ ሁኔታ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ባለማወቅም ሆነ በቸልተኝነት *መቃሲድ* ግንዛቤ ውስጥ የማይገባበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሕግ ባለሙያዎችና ተከራካሪ ወገኖች የግል ወይም የደንበኞቻቸውን ጥቅም ለማስከበር ሲባል በሕጎች አተረጓጎም ላይ ብልሐተኛ (*ሥልታዊ*) *(ሂያል)* በመሆን ሲባል ሕግ ተጠምዝዞ የሚተረጎምበት፣ ወደ ግቡ የሚደርስበትን አቅጣጫ እንዲስት የሚደረግበት ዘዴ፣ በ*መቃሲድ* የሚታረም መሆኑ፣ በርዕሱ ላይ በቂ ግንዛቤ መያዝ አንገብጋቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም፣ *መቃሲድ* የሸሪዓ ሕግን በትክክል ለመረዳት እና ተግባራዊ ለማድረግ ካለው መሠረታዊ ጠቀሜታ አኳያ፣ ምንነቱን፣ የሕግ ዓላማዎች የሚለዩባቸው ዘዴዎችን፣ ልዩ ልዩ የ*መቃሲድ* አመዳደቦችን፣ ጠቅላላ የሸሪዓ ዓላማዎችን እና ሌሎች መሠረታዊ ፍሬ-ሐሳቦች በዚህ ጽሁፍ ርዕሶች ሥር ተቃኝተዋል፡፡

## 1. የ*መቃሲድ* ታሪካዊ እድገት

*መቃሲድ* እንደ ሌሎቹ የታወቁ የ*ኡሱል አል-ፊቅሕ* አርዕስት ሁሉ ከጥንታዊ የመስኩ አነሳስ ጀምሮ የነበረ ሳይሆን የቅርብ ዘመናት *ኡሱል* ምሁራን ትኩረት ያገኘና የ*ኡሱል* ጥናት ዘርፍ አዲስ ጭማሬ ነው፡፡ በዚህ ዘመን የሚወጡ ብዙዎቹ የ*ኡሱል* ድርሳናትም ቢሆኑ የ*መቃሲድ* ርዕስን አካተው አይገኙም፡፡[5] ምንም እንኳ ግንባር ቀደም የሙሀመድ ባልደረቦች፣ ሸሪዓን እንድ ሕግ ብቻ ሳይሆን እንደ ሥርዓተ-እሴት ይመለከቱት የነበር ለመሆኑ፣ እና እነዚህ እሴቶችንና ዓላማዎችን በሕግ አተረጓጎማቸውና ትግበራቸው ላይ ያንጸባረቁ መሆኑን የሚያስረዱ ታሪካዊ ማስረጃዎች ቢኖሩም፣ በመጀመሪያዎቹ የኢስላም ዐሥርተ-ዓመታት በባልደረቦች ተከታዮች *(ታቢዑን)* ተመስርተው ከነበሩ ሁለት የምሁራን ጎራዎች፣ *አሕል አል-ሀዲስ* (የ*ሀዲስ* ባለቤቶች) የሚባሉት፣ ከ*አሕል አር-ረእይ* (የእሳቤ/አመክንዮ ባለቤቶች) አንጻር ሲታዩ፣ በቀዳሚ ምንጮች (ቁርአንና *ሱናሕ)* የተደነገጉ ሕጎችን *ቃል-በቃል* የመተርጎም ዝንባሌ የነበራቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በተቃራኒው ዓላማን ወይም ምክንያታዊ እሳቤን በምንጮች ያልተደገፈ ነው በማለት ይቃወሙ የነበር መሆናቸዉ፣ *መቃሲድ* በእነዚህ የእድገት ጊዜያት መሠረት እንዳያገኝ ሆኗል፡፡[6] ከእነዚህ የምስረታ ዘመናት በኋላ ለሦስት ምዕተ-ዓመታት የዘለቀው የሸሪዓ አረዳድ ዋነኛው መገለጫው ደረቅ፣ የቃል በቃል የሕግ አረዳድ ዘዴዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ የሸሪዓ ዓላማዎች ግምት ውስጥ ሳይገቡ ሕጎችን የሚተረጉሙትና ከምንጮቹ የሚወስዱበት *(ኢጅቲሓድ)* አቀራረብ ሰፍኖ ነበር፡፡[7]

ከዟሒሪዎች በስተቀር፣ ሁሉም *ኡሱል* ምሁራንና *መዝሓቦች፣ የመቃሲድን* አስፈላጊነትና ጠቀሜታ በእጅግ ያምኑበት ነበር፤ በተጨባጭ የሕግ ትንታኔያቸው፣ ከሸሪዓና የ*ፊቅሕ*

[5] Mohammad Hashim Kamali, "Maqasid Al-Sharī'ah": The Objectives of Islamic Law, Islamic Studies, Vol. 38, No. 2, p. 198. Available At: Http://Www.Jstor.Org/Stable/20837037 (Accessed: 20-10-2017).

[6] Kamali, *"Maqasid Al-Sharī'ah"*, *Supra* note 5, p. 198.

[7] Ibid.

ድንጋጌ ምክንያት *(ዒላሕ)* እና ዓላማ ጋር የሚጻረር አተረጓጎምን አይቀበሉም ነበር።[8] ሆኖም ግን እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ *መቃሲድን* በርዕስነት አንስተው ለማብራራት ዝግጁ አልነበሩም፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በምርምር አማካይነት የሕግ አውጪውን ትክክለኛ ዓላማ ላይ መድረስ ለመለየት የማይቻል በመሆኑና፣ በመለየቱ ሂደት ውስጥ በማናቸዉም ሁኔታ እርግጠኛ መሆን የማይቻልበትና በጥርጣሬ ወይም ግምታዊነት *(ዞኒ)* ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ፣ የሸሪዓ ሕግጋት በ*መቃሲድ ሥም* አተረጓጎማቸው እና አፈጻጸማቸው የሚሸረሸርበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል በሚል *ሥጋት* ርዕሱ ለረዥም ክፍለ-ዘመናት የጥናት የምርምር ትኩረት እንዳያገኝ ሆኗል።[9] ይህ *ሥጋት መቃሲድ ኢጅቲሓድን* በትክክለኛ ጎዳና ላይ እንዲራመድ በማድረግ ካለው ወሳኝ ሚና አኳያ፣ *መቃሲድን* ወደጎን ለማለት በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም። *መቃሲድ* ተገቢነት በሌለዉ የግል ጥቅም ወይም ቡድናዊ እሳቤ ምክንያት የሕግ ማቅለያ ወይም ማሻሻያ ከሚሆንበት እድል በላይ የሸሪዓ ሕግጋት ከጠቅላላ የ*መስላሃሕ* ሸሪዓ ዓላማ እና በተለየ የተደነገጉበትን ልዩ ዓላማ በሳተ አኳኋን የሕግ አዉጪዉን ሐሳብ በሚያደናቅፍ እና በማያሳካ ዘዴ እንዲተረጎሙ የሚሆኑበት አደጋ የከፋ ነው፤ በተለይም ላልተገባ የሕግ አክራሪነት/አጥባቂነት *(Legalism)* ጽንፍ የሚጋብዝ ነው፤ የዘመናችን የ*ፊቅሕ* አስተማሪዎች፣ ሰባኪዎችና ሰፊው ማህበረሰብ የሕግ አተኳሪነት *(Literalist legalism)* ባህል የዚህ ታሪካዊ እድገት ውጤት ነው።[10]

በሸሪዓ እድገት ታሪክ፣ የ*መቃሲድ* ሐሳብ የተነሳውና ፈር-ቀዳጅ ሐሳቦችን በድርሳኖቻቸው ያንሸራሸሩት ምሁራን በ10ኛው ክፍለ-ዘመን፣ በአት-ተርሚዝ አል-ሃኪም (932 ኢ.) ሲሆን፣ ይህን *ሥራ* ያጣቀሰ ሌላ የ*መቃሲድ ሥራ* በኢማም አል-ሃረመይን አል-ጁወይኒ (1085 ኢ.) ተደርሷል።[11] አል-ጁወይኒ የቁርአን እና የ*ሱናሕ* ሕጎችን በጥልቀት በማጥናት እና ከጀርባቸው የያዙቱን አንኳር እሴቶች (ዓላማዎች) በመፈተሽ አጠቃላይ የሸሪዓ ዓላማዎችን ለይተዋል፤ በብዙኃኑ ዘንድ ተቃባይነት ለማግኘት የቻለውን፣ የ*መቃሲድ ሦስትዮሽ* አመዳደብን፣ ማለትም መሠረታዊ ፍላጎቶች *(ደሩሪያት)፣* ደጋፊዎች (አባሪዎች) *(ሃጂያት)* እና አሳማሪዎች (ቅንጦታዉያን)፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቁት ጁወይኒ እንደሆኑ ይታመናል።[12] ከጁወይኒ በኋላ የ*መቃሲድን* ጽንሰ-ሐሳብ እና የጥናት ዘዴዎች በማስፋፋት፣ አልገዛሊ (እ.አ.አ 1111 ኢ.) *‹ሺፋዕ አል-ገሊል›* እና *‹አል-ሙስተስፋ›* በተሰኙ መጽኃፎቻቸው ጠቃሚ *መቃሲድ* ምልከታዎችን አክለዋል። ሸሪዓ፣ እምነት፣ ሕይወት፣ አዕምሮ፣ የዘር-ሐረግ - ተወላጆችን *(ነስል፣ ነሰብ)* እና ንብረት የተሰኙ አምስት መሠረታዊ ዓላማዎችን የያዘ መለኮታዊ የሕግ ማዕቀፍ እንደሆነ፣ ከምንም በላይ እነዚህ ዓላማዎች ቅድሚያ ሊሰጣቸው እና ጥበቃ ሊደረግባቸው እንደሚገባ በ*ሥራዎቻቸው* አጽንኦት ሰጥተዋል።[13]

ከዚህ በኋላ የመጡ የልዩ ልዩ *መዝሓብ* ሊቃውንት በተጀመረው የ*መቃሲድ* እሳቤ ላይ ታካይ ጥናት በማድረግ *መቃሲድ* የየራሳቸውን ምልከታዎች ጨምረዋል። ለአብነት ያህል፣ በሁለት

---

[8] Ibid., pp. 198-199.

[9] Ibid., p. 199.

[10] Mohammad Hashim Kamali, Sharia Law: An Introduction, Oxford፡Oneworld Publications, Oxford, 2008, p. 125.

[11] Kamali, *"Maqasid Al-Sharī'ah", Supra* note 5, p. 199.

[12] Ibid.

[13] Ibid.

*የቂያስ* (ምስስሏዊ አመክንዮ) መካከል ግጭት ቢፈጠር፣ *መቃሲድን መሠረት ያደረገ ምርጫ (ተርጂሕ)* ማድረግ ይገባል በማለት ፈኽር አድ-ዲን አር-ራዚ (1208 አ.) እና ሰይፍ አድ-ዲን አል-አሚዲ (1233 አ.) በማለት *መቃሲድ* በ*ኢጅቲሓድ* ላይ ሊኖረው ከሚገባው ሚናዎች መካከል አንዱን ጠቁመዋል፤ በተጨማሪም በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ሸሪዓዊ የሕግ ዓላማዎች መካከል አንዱን መምረጥ ግድ ሆኖ ከተገኘ፣ አንዱ ከሌላው ሊመረጥ የሚችልባቸዉን መመዘኛዎች አብራርተዋል፡፡[14] የማሊኪ *መዝሓብ* ሊቅ የሆነው ሺሓብ አድ-ዲን አል-ቀራፊ (1285 አ.) ደግሞ የሸሪዓ ድንጋጌዎችን ተመርኩዞ ከላይ አል-ገዛሊ ከለዩዋቸው አምስት መሠረታዊ የሸሪዓ ዓላማዎች በተጨማሪ፣ ክብር *(አል-ዒርድ)* ስድስተኛ የሸሪዓ ዓላማ ሆኖ ሊታከል እንደሚገባ አስገንዝቧል፤ ለዚህ የአል-ቀራፊ ሐሳብ፣ ከእርሱ በኋላ የመጡት አስ-ሱብኪ (1834 አ.) እና አሽ-ሸዉካኒ (1834 አ.) ድጋፍ ሰጥተዋል፡፡[15] በተጨማሪም፣ ዐብድ አሰ-ሰላም አስ-ሱላሚ (1282 አ.) ደግሞ፣ በ*መቃሲድ* ላይ በሚያተኩረዉ *‹ቀዋዒድ አል-አህካም›* *ሥራቸው*፣ በዒላሕ እና *መቃሲድ* ዙሪያ ተጨማሪ አዲስ ሐሳቦችን ያመነጩ ሲሆን፣ ከሀሉም የቁርአን ዓላማዎች ቀዳሚው ‹ጉዳትን መከላከልን› ጨምሮ በየትኛውም ገጽታው ‹ጥቅምን ማስገኘት/ማስከበር› ነው በማለት ሰፋ ያለ ምልከታ አስተዋውቀዋል፡፡[16] አል-ሻጢቢ (1388 አ.) ደግሞ ቀድመው የተነሱ የ*መቃሲድ* ንደፈ-ሐሳቦችን በጥልቀት በመተንተንና አዲስ የእይታ አቅጣጫዎችን በማመላከት፣ እንዲሁም *መቃሲድ* ከሚለይበቸው ዋነኛ ዘዴዎች መካከል አንዱና ዋነኛ የሆነውን ዳሰሳዊ/ሁለንተናዊ የሕግ ምርምር *(ኢስቲቅራእ/Induction)* ዘዴ በማስተዋወቅ፣ለ*መቃሲድ* እድገት የጎላ ምሁራዊ አበርክቶ ያደረጉ ከመሆኑ አንጻር፣ የ*መቃሲድ* አባት *(ሸይኽ አል-መቃሲድ)* የሚል መጠሪያ ሊያገኙ ችለዋል፡፡[17]

እንደ ተቂይ አድ-ዲን ኢብን ተይሚያሕ ደግሞ የሸሪዓ ዓላማዎች ከላይ በተወሱት ጥቂት ዓላማዎች ብቻ ሊወሰን አይችልም፤ ሌሎችን ለምሳሌ፣ ዓለማዊ ሕይወትን በሚመለከት የውል ግዴታን ማሟላት፣ የዝምድና ትስስር መጠበቅ፣ የጎረቤት መብትን ማክበር ወዘተ..፣ ዘልዓለማዊ ሕይወትን በሚመለከት አምላክን ማፍቀር፣ ቅንነት፣ መልካም ባህርይና ሥነ-ምግባር ወዘተ..፣ ከብዙዎቹ የሸሪዓ ዓላማዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡[18] ይህ የሸሪዓ እሴቶች ውሱን ያለመሆን ሐሳብ አህመድ ረይሱኒን ጨምሮ ሌሎችም ዘመነኛ የ*መቃሲድ* ምሁራን ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡[19] ከዚህ እሳቤ ላይ፣ የሰብዓዊ መብት እና ነጻነቶች ጥበቃ፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ ምርምር እና ልማት፣ በብሔሮች መካከል ሰላማዊ እና በመከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ማረጋገጥ የመሳሰሉት ከቁርአን እና ከሱናሕ ድጋፍ የሚገኝላቸዉ ታላላቅ *መቃሲድ* ናቸው በማለት ፕሮፌሰር ሙሀመድ ሐሺም ከማሊ የራሳቸውን ሐሳብ ጨምረዋል፡፡[20] ባጠቃላይ የሸሪዓ ዓላማዎች

---

[14] Ibid.

[15] Ibid., pp. 199-200.

[16] Mohammad Hashim Kamali, Goals and Purposes *(Maqasid)* of Shariah (Part 1), IAIS Bulletin on Islam and Contemporary Issues, No. 31 March-April 2016, p. 3. Available at: https://www.iais.org.my/e/attach/bulletin/2016/bulletin31.pdf (Accessed: 10-Nov-18). see also: Kamali, *"Maqasid Al-Sharī'ah", supra* note 5, p.199.

[17] Ibid., See also: Kamali, *"Maqasid Al-Sharī'ah", supra* note 5, 198.

[18] Kamali, *"Maqasid Al-Sharī'ah", supra* note 5, p. 200.

[19] Ibid.

[20] Ibid., p. 201.

በጥቂት ዓላማዎች ሊገደብ የማይችል፣ እንደ ወቅታዊ እና አካባቢያዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ዓላማዎቹ ጎልተው ሊወጡ እና ሊታዩ የሚችሉ በመሆኑ የ*መቃሲድ* በር ሁልጊዜም ክፍት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡[21]

## 2. ጠቅላላ የሸሪዓ ግቦች *(መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ)*

ኢስላም በእምነት *(ዓቂዳሕ)* እና በሸሪዓ ማዕቀፉ፣ የሰው ልጅ በምድራዊ እና ከሞት በኋላ ባለው ሕይወቱ ስኬታማ እንዲሆን የማድረግ ዓላማ ያነገበ አምላካዊ መመሪያ ነው፡፡ በሸሪዓ ማዕቀፉ በተለየ ደግሞ በዋናነት ሰው በዚህ ዓለም በሚኖረው ቆይታ በግለሰባዊ ሕይወቱ ደስተኛና የተረጋጋ እንዲሆን፣ በማህበረሰብ ወይም በሃገር ደረጃ ያለውን ዘርፈ-ብዙ መስተጋብር ሰላማዊና ፍትሐዊ እንዲሆን በሚደረገው ውጣ-ውረድ ውስጥ ተዓማኒ እና ፍሬያማ የሆኑ መለኮታዊ የሕግ መርሆዎችን እና ድንጋጌዎችን ያቀርባል፡፡ ኢስላም፣ የሸሪዓ ሕግን የበላይነትና መሪነት በማስፈን ከሰብዓዊ ጥረት በላይ መለኮታዊ የሕግ እውቀትንና ጥበብን በመለገስ የፍትሕ፣ የሰላም እና የልማት ዓላማዎችን የማሳካት ግብ ያለው ነው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች እውን ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ፣ ሰው በተሰጠው የማሰብ አቅም እና ነጻ-ምርጫ የራሱን ሰብዓዊ የሕግ ምርምር ሲያደርግ የቆየ እና አሁንም በማድረግ ላይ ያለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጥረቱ መለኮታዊ እገዛ እና አመራር ታክሎበት ወደ አስተማማኝ ሁኔታ ወደ ስኬቶቹ እንዲያመራ ያስችለዋል፡፡ ሰው ለሸሪዓው በቀረበው ልክ ለስኬቶቹም ያንኑ ያህል ይቀርባል፤ ከራቀም ያንን ያህል እየራቀ ይሄዳል፡፡ ኢስላም ምድራዊ ዓላማዎችን በማንገብ እና የሰውን እርምጃ ከፊት ሆኖ ከመምራት ዓላማው በተጨማሪ፣ እነዚህ ምድራዊ ስኬቶች ተደምረው ወደ ዋነኛዉ የቀጣዩ ዓለም ስኬት ግብዓት እና መጋቢ የሚሆኑበትን የእምነት ማዕቀፍ ይዘረጋል፡፡ በሌላ አገላለጽ ሸሪዓዊ ግቦች ለመንፈሳዊ ግቦች እውን መሆን መሳሪያዎች ናቸው፤ ስለሆነም ሸሪዓ በሕግነቱ ግለሰባዊ ሕይወትን፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስተጋብሮችን ከመቆጣጠር እና ምድራዊ ስኬትን እንዲቀዳጅ ከማድረግ በላይ የእነዚህ ስኬቶች ድምር ለመጪው ሕይወት መሳካት እና ማማር መሳሪያዎች ናቸው፡፡[22] ይህ መንፈሳዊ ዓላማ ከሸሪዓ ዓላማዎችም በላይ ታላቁ የኢስላም ዓላማ መሆኑን የሸሪዓ ሊቃዉንት ያስገነዝባሉ፡፡[23]

---

[21] Kamali, Sharia Law, *supra* note 10, p. 127.

[22] ለመለኮታዊ ሕጎች ተከታይ እና ታዛዥ መሆን ከሰው አዕምሯዊ ግኝቶች በላይ ፍሬያማ ረቂቅ ጥበብ እና ፋይዳ ያዘሉ ከመሆናቸዉ በተጨማሪ የእምነት ነጸብራቅ ናቸው፡፡ አንድ ሰው፣ ማህበረሰብ ወይም ሃገር በሸሪዓ ሲተዳደር ከምድራዊ ጉልህ ፋይዳዉ ባሻገር ከሰው እዉቀት እና ጥበብ በላይ ላለ ሌላ ታላቅ የሕግ እውቀት እና ጥበብ ያለ መሆኑን እውቅና እየሰጠ ነው፤ ተገዢነቱን፣ እጅ መስጡቱን በአመለካከት ከሚይዘዉ በላይ በተግባር እያሳየ ነው፡፡

[23] Mohammad Hashim Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *Islamic Quarterly*, p. 119, Available At: http://www.hashimkamali.com/index.php/publications/item/113-sources-nature-and-objectives-of-the-sharicah (Accessed on: 24, Nov, 2017).

ኢስላም እንደ ወጥ የሕይወት መመሪያ ወይም ቁርአን እንደ በላይ የእዉቀት ምንጭ፣ ዋነኛ ትኩረቱ ዓለማዊ ሕይወትን ስኬታማ በማድረግ የቀጣዩን የድሕረ-ሕልፈት ዘልዓለማዊ ሕይወት ማሳካት ነው፤ ስለሆነም የሸሪዓ ሕጎች በየደረጃው የራሳቸው ዓላማ እና ለጠቅላላው የሸሪዓ ሕግ ማዕቀፍ የተለዩ ግቦች ቢኖሩም፣ የኢስላም የመጨረሻ ዓላማዎች ናቸው ማለት አይደሉም፡፡ ለዚህ አብነት የሚሆነዉ፣ ይህን በቀጥታ የሚያረጋግጡ በርካታ የቁርአን ጥቅሶች ከመኖራቸዉም በላይ፣ ከአጠቀላይ የቁርአን 6235 አንቀጾች መካከል፣ ወደ 350 ብቻ የሚሆኑትን ሕግን የተመለከቱ መሆኑና፣ ሌላው የቁርአን ክፍል በጥቅሉ ስለእምነትና እና ቀጣዩ ዓለም የሚያጠነጥን መሆኑ ነው፤ በዚህም መሠረት ቁርአን እንደ ሕግ መጽሓፍ ሊወሰድ አይችልም፣ በራሱ በመጽሓፉ አነጋገር፣ ቁርአን የሕይወት ‹መመሪያ *(ሁዳ)*›፣ የዋነኛው ግብ ‹አስታዋሽ፣ ተግሳጽ *(ዚክር)*፣ በተሰኙ ስሞች ይጠራል፡፡ (See: Kamali, Sources, *supra* note 22, p. 119).

በሰው የሕግ ምርምር አማካይነት የሕግ ሥርዓትን ሊዘረጋ የሚችልበት አቅም ቢሰጠውም፣ የምሉዕ እዉቀት ባለቤት አይደለም ተብሎ ስለሚታመን ጥቅል የሕግ መርሆዎች እና ማሳያ ድንጋጌዎች በቁርአን እና በ*ሱናሕ* ተገልጸው እናገኛለን፡፡ እነዚህ መለኮታዊ የሕግ መርሆዎች ለሰው የሕግ እዉቀት ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* መሪ እንደመሆናቸው የመለኮታዊ እዝነት መገለጫዎች እንደሆኑ የእምነቱ ተቀዳሚ ምንጮች ያስረዳሉ፤ ለዚህም ነው ኢስላም የእምነት ክፍሉ እንዳለ ሆኖ፣ በሸሪዓ ክፍሉ ለአማኞች መመሪያ እና እዝነት እንደሆነ ቁርአን በምዕራፍ 10 አንቀጽ 57 የሚገልጸው፡፡ በዚህ ረገድ የመልዕክቱ አምባሳደር የሆኑት ነቢዩ ሙሀመድ ራሳቸው አምላካዊ እዝነት የተገለጠባቸው ልዑክ መሆናቸውን ቁርአን ያስረዳል፡፡[24]

ጠቅለል ባለ አቀራረብ፣ ሸሪዓ እንደ መለኮታዊ የሕግ ማዕቀፍ፣ የሰውን ምድራዊ እና ድሕረ-ሕልፈት ስኬት ለማረጋገጥ ሲል በሕግ ማዕቀፉ ውስጥ ተሰራጭተው የሚገኙት ዓላማዎቹ በሦስት መሠረታዊ ዓላማዎች ስር ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡ እነዚህም፣ አንደኛ፣ ግለሰባዊ ሰብዕናን ማነጽ *(ተሕዚብ አል-ፈርድ)*፤ ሁለተኛ፣ ፍትሕን *(ዐድል)* ማስፈን፣ እና ሦስተኛ፣ የሰዎችን ጥቅም ማረጋገጥ *(መስለሃሕ)* ናቸው፤[25] እነዚህ ዓላማዎች በተከታዮቹ አንቀጾች ተብራርተዋል፡፡

በ*ተሕዚብ* ስር ያለው የሸሪዓ ዓላማ የማህበረሰቡ አባላት የሆኑትን ግለሰቦች አመለካከት እና ሥነ-ምግባር በማነጽ ሕብረተሰቡን በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ግንኙነቱ ሚዛናዊ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡[26] ማህበረሰብ የግለሰቦች ድምር ውጤት እንደመሆኑ፣ ሰዎች በተናጠል ያላቸውን ሰብዕና በሥነ-ምግባር እና መንፈሳዊ ትምህርት በማነጽ፣ የሕብረተሰቡን የግብረ-ገብ ዕሴቶች፣ የመከባበርና የሰላም እሴቶችን መጠበቅ ይቻላል፡፡[27] በሌላ በኩል ግለሰቦች በቁሳዊ ሕይወታቸው ራሳቸውን ከመቻል ባለፈ፣ ለቤተሰባቸው፣ ለማህበረሰባቸው፣ ብሎም ለሃገር ጠቃሚ እና የራሳቸውን ሚና ማከል የሚችል ይሆኑ ዘንድ በልዩ ልዩ የቁሳዊ የሳይንስ ትምህርት መስኮች በእውቀትና በሙያ የተካኑ እንዲሆኑ ለማድርግ፣ አጠቃላይ የሸሪዓ ምድራዊና መንፈሳዊ ዓላማዎችን ለማሳካት ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ በዚህ ረገድ፣ በዓለም የሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ ለዘመናት የዘለቀውን የሃይማኖት ትምህርትና የምድራዊ ሳይንሶች ክፍፍል *(Educational Dualism)*፣ እንዲሁም በሳይንስ የእዉቀት ዘርፎች ላይ የታየው ደካማ የሙስሊሞች ተሳትፎ፣ እና ዓለማዊ ሳይንሶች ከመለኮታዊ የእውቀት ማዕቀፍ ውጪ በራሳቸው መንገድ በመፈርጠጣቸው ምክንያት የደረሰውን ዓለም-አቀፍ የሰብዓዊነት መንጠፍ፣ ቁሳዊነትና አፍቅሮ-ትፍስህት፣ የሰላምና መረጋጋት እጦት ወዘተ.. ችግሮችን ለመቅረፍ፣ የዘመኑ የሙስሊምና ሙስሊም ያልሆኑ የሥነ-ትምህርት ልሂቃን፣ እውቀትን ኢስላማዊ ለማድረግና *(Islamization of knowledge)* የሁለትዮሽ የትምህርት አቀራረብ ችግሮችን ለመቅረፍ ከፍተኛ ምሁራዊ ጥረት በማድረግ

---

[24] Ibid., p. 225፣ ‹‹(*ሙሐመድ ሆይ!*) *ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡››*(ቁርአን፡ 21፡107)

[25] Ibid.

[26] Ibid.

[27] Ibid.

ላይ ይገኛሉ።[28] ይህም ግለሰቦችን በትክክለኛው የሸሪዓ እውቀት እና እሴቶች በማነጽ፣ የሸሪዓ ዓላማዎችን ከግብ በማድረስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።[29]

ቁርአናዊው የፍትሕ ጽንሰ-ሐሳብ ሰፊ ሲሆን የበደል ቀጥተኛ ተቃራኒ የሆነውን የእርምት ወይም ቅጣት-ተኮር ፍትሕ *(corrective or retributive justice)* ብቻ ሳይሆን፣ በርትዕ *(ኢህሳን)* እና በእኩል ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ፍትሕ *(distributive justice)* የማስፈን ዓላማ አለው።[30] የፍትሕ ዓላማ በኢስላም ወይም በመጨረሻው የአምላክ ነቢይ በሆኑት በሙሀመድ እና በሕዝባቸው ላይ ብቻ የተደነገገ ሳይሆን፣ ሁሉም የቀደምት የአምላክ መልዕክተኞች ያነገቡት እና እውን ለማድረግ ከፍተኛ ተጋድሎዎችን ያደረጉበት፣ ከአምላክ የተደነገገ ታላቅ የተልዕኮ ግብ ነው።[31] ሕግን ተፈፃሚ በማድረግ ፍትሕን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ውጤቱ የሕጉን ዓላማ የማያሳካ በሚሆን ጊዜ በአተረጓጎሙ ዓላማውን በማገናዘብ ከፍትሕ በተጨማሪ ርትዕ *(ኢህሳን)* እውን የሚደረግበት ማዕቀፍ ያለው ነው።[32]

ሌላኛው የሸሪዓ ዓላማ የሰዎችን ጥቅም *(መሷሊሕ)* ማስጠበቅ ነው። ጥቅም ሲባል የትኛውንም አይነት ፋይዳ የሚያካትት ሲሆን፣ ምድራዊ እና ከሕልፈት በኋላ ያለውን፣ የግለሰብን እና የማህበረሰብን ቁሳዊ፣ ሞራላዊ እና መንፈሳዊ እንዲሁም የዚህን እና የመጪዉን ትውልድ ጥቅም በሙሉ አካቶ የያዘ ሰፊ ጽንሰ-ሐሳብ ነው። በዚህ ዓላማ ሥር ጉዳትን ወይም ብልሹነትን *(መፍሰዳሕ)* መከላከል ይካተታል፤ ምክንያቱም ጥቅሞችን የሚያሰናክሉ ወይም ጉዳትን የሚያስከትሉ ችግሮች ባሉበት *መስላሃን* እውን ማድረግ የማይቻል በመሆኑ ጉዳትን መከላከል *(ደፍዕ አድ-ዶረር)*[33] ወይም ችግርን ማስወገድን *(ረፍዕ አል-ሀረጅ)*[34] በራሱ ጥቅምን የማስገኘትና የማረጋገጥ አካል ነው።[35] *መፍሰዳሕን* መከላከልና

---

[28] Taha Jabir Alwani, Toward An Islamic Alternative in Thought and knowledge, The American Journal of Islamic Social Sciences, Vol. 6, N0. 1, 1989, pp 3-4, Available at: https://i-epistemology.net/subjects/islamization-of-knowledge/item/333-toward-an-islamic-alternative-in-thought-and-knowledge.html (Accessed: 10-Nov-18).

ከጥቂት ዐስርተ-ዓመታት ወዲህ፣ እውቀትን ኢስላማዊ ስለማድረግ እና የሁለትዮሽ የትምህርት ሥርዓት በሙስሊሙ ዓለም የመስኩ ምሁራን እና የምርምር ተቋማት አማካይነት አበረታች የሆነ የሥነ-ጽሁፍ እድገት እየታየ ሲሆን፣ ከኢስላማይዜሽን መርሆዎች እና ዘዴዎች በተጨማሪ፣ በርካታ የተፈጥሮ እና የማህበረሰባዊ ሳይንሶች እንደገና በኢስላማዊው የሥነ-እውቀት ፍልስፍናና ምንጮች እየተቃኙ ይገኛሉ። ለዚህም፣ ፊር-ቀዳጅ ከሆነው የኢስላማይዜሽን አባት ተብሎ ሊጠቀስ በሚችለው ታላቁ ምሁር ዶ/ር ኢስማዒል አል-ፋሩቂ የተቋቋመውን ዓለም-አቀፍ የኢስላማዊ እሳቤ ተቋም (The International Institute Of Islamic Thought (IIIT) ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ ኢስላማዊ የትምህርትና የምርምር ማዕከላት ለዘርፉ እድገት ከፍተኛ ምሁራዊ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ የኢስማዒል አል-ፋሩቂ ፋና-ወጊ የሆነው፣ ‹Islamization of Knowledge: Gneral Principles and Work plan.› የተሰኘውን ሥራ ይመለከቷል (Available at: https://www.muslim-library.com/dl/books/English_Islamization_of_Knowledge_General_Principles_and_Work_Plan.pdf ላይ ይገኛል)፤ እንዲሁም የ IIIT ድረ-ገጽ https://iiit.org/en/home/ እና https://i-epistemology.net/ ይጎብኙ። ከኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ አንጻር፣ ኢስላማይዜሽን በሐሳብ ደረጃ በቂ ግንዛቤ መጨበጥ አስፈላጊ ቢሆንም፣ ከዚህ በፊት ጥንታዊው ኢስላማዊ ትምህርት ላይ ሥር-ነቀል ማሻሻያ እና ለውጥ ሊደረግበት መሆኑን በመጠቆም፣ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያን ሙስሊም ማሕበረሰብ ተጨባጭ እውነታዎች መሠረት ያደረገ ኢስላማዊ የሥነ-ትምህርት ምርምር ሊደረግ ይገባል።

[29] Kamali, Sharia Law, *supra* note 10, p. 28.

[30] Kamali, Sources, *supra* note 22, p. 225.

[31] Ibid., p. 227. እንዲሁም ቁርአን፣ *አል-ሀዲድ፣* 5፡25 ይመለከቷል።

[32] Ibid. እንዲሁም ቁርአን፣ *አል-ነህል* 16፡90 ይመለከቷል።

[33] ቁርአን፣ *አል-ሐጅ፣* 22፡78

[34] ቁርአን፣ *አል-ማኢዳሕ፣* 5፡6፣ አን-ኒሳእ፣ 4፡28.

[35] Kamali, Sharia Law, *supra* note 10, p. 132.

ማስወገድ የጠቅላላው የሸሪዓ ሕግ ማዕቀፍ መዘርጋት ታላቅ ምክንያት *(ዒላሕ)* ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡[36] በዓለማዊ ሕይወት ውስጥ በጥቅሉ ለሰዎች ጠቃሚ የሆነውን *(መስላሃን)* እና ጎጂ የሆነውን *(መፍሰዳሕን)* በተጠየቃዊ የአዕምሮ ምዘና መለየት የሚቻል ሲሆን፣ በዚህ የግምገማ ሂደት ላይ ግላዊ ጥቅም እና ስሜት ከሚዛናዊ የ*መስላሃሕ* እሳቤ ጋር እንዳይቀላቀል ለመጠበቅ ሲባል ሸሪዓ ጥቅል መርሆዎችን የሚዘረጋ ቢሆንም፣ ጥቅም እና ጉዳትን የመለየት ዋነኛ ድርሻ ለኢጅቲሓድ የተተወ ነው፡፡[37]

አሽ-ሻጢቢ *‹አል-ሙዋፈቃት ፊ ኡሱል አሽ-ሸሪዓሕ›* በተሰኘው ፋና-ወጊ መጽሃፋቸው እንደገለጹት፣ ኢስላም በሕግነት (ሸሪዓ) ቅርጹ ለሰው ምድራዊ ፋይዳ ሲባል የተዘረጋ፣ የፈጣሪ እዝነት *(ረህማሕ)* መገለጫ ነው፡፡ *ዋጂብ*፣ *መንዱብ* እና *ሙባህ* የሕግ ቅርፆች አዎንታዊ ፋይዳን ወይም ጠቀሜታን *(መስለሃሕ)* እውን የማድረግ ዓላማ ያላቸው ሲሆን፣ *ሀራም* እና *መክሩሕ* ደግሞ ጉዳትን ወይም ብልሹነትን *(መፍሰዳሕ)* ለመከላከል የተደነገጉ ናቸው፡፡[38] ዝርዝር የሸሪዓ ድንጋጌዎችን በማስፈጸም ሂደት ውስጥ አንዱ ከሌላው ጋር የሚጋጭበት አጋጣሚ ቢፈጠር በይበልጥ *መስለሃሕ* የሚያስገኘው ተመራጭ መሆን ይገባዋል፡፡ ይህም ከላይ ሕግን ከርትዕ *(ኢህሳን)* የሸሪዓ ዓላማ ጋር እንደሚተረጎመው ሁሉ ሕግጋትን በመፈጸም ውስጥ የግድ አንዱ መመረጥ ካለበት በይበልጥ ጥቅም በሚያስጠብቅ አኳኋን እንዲሆን ማድረግም እንዲሁ ሌላው የሸሪዓ ዓላማ ነው፡፡[39]

የሰው ጥቅም *(መሷሊሕ)* በጥቅሉ በሦስት ይከፈላል፤ እነሱም መሠረታዊ አስፈልጎቶች *(ዶሩሪያት)*፣ ማሟያዎች *(ሀጂያት)* እና ቅንጦቶች *(ተህሲኒያት)* ናቸው፡፡ ሸሪዓ በየትኛውም ቅርጹ ከእነዚህ ጥቅሞች አንዱን እውን የማድረግ ዓላማ አለው፡፡ የ*ዶሩሪያት* አስፈልጎቶች የሰው ሕልውና የተመሠረተባቸው፣ የሕይወት፣ የእምነት፣ *ሥነ*-ልቦና እና ንብረት ፍላጎቶች ሲሆኑ፣ የእነዚህ አለመሟላት ወይም መጓደል ሁለንተናዊ ቀውስ እና ማህበረሰባዊ ዝንፈት የሚያስከትል በመሆኑ ሸሪዓ ልዩ እና የከረረ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ የ*ሀጂያት* ጉዳዮች ደግሞ ከላይ ወሳኝ ለሆኑት አስፈልጎቶች መከበር አባሪ ሲሆኑ፣ የእነዚህ መሟላት ለ*ዶሩሪያት* መከበር ደጋፊ ሚና አላቸው፡፡ የ*ሀጂያት* አለመሟላት ወይም አለመከበር ማህበረሰባዊ ቀውስን የማያስከትል ቢሆንም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን፣ ጉዳትን ወይም እንግልትን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ ሸሪዓው በ*ዒባዳት* ወይም በ*ሙዓመላት* ክፍሉ ያካተታቸው የሕግ ማቅለያዎች በሙሉ በ*ሀጂያት* *ሥ*ር የሚወድቁ ናቸው፣ ለመንገደኛ ወይም ለታማሚ ሰው የተፈቀዱ የአምልኮ ማቅለያዎችን አለመጠቀም መቸገርን *(ሀረጅ)* ያስከትላሉ፡፡[40]

የ*መሷሊሕ* አወሳሰን በጠቅላላው ሰዎችን በተጨባጭ ይጠቅማል በሚል *(ሃቂቂያሕ)* እሳቤ ላይ የሚመረኮዝ እንጂ የግለሰቦች ጥቅም እና ምቾት *(መናፊዕ)* ግምት ውስጥ ሊገባ አይችልም፡፡ ከተጠየቃዊ እና ገለልተኛ ምዘና ውጪ *መስላሃሕ* በግል ፍልጎትና *ሥሜት(አህዋእ አን-ኑፉስ)* እና ወገንተኛ ታሳቢዎች ላይ የተመሠረተ ከሆነ የሁለንተናዊነት *(Universal)* ባህርይውን የሚያሳጣው ይሆናል፡፡[41] በተጨማሪም፣ በ*መስላሃሕ* አወሳሰን

[36] Ibid., p. 36.

[37] Kamali, Sharia Law, *supra* note 10, p. 35.

[38] Ibid., p. 132

[39] Kamali, Sources, *supra* note 22, p. 230

[40] Ibid., p. 229

[41] Ibid.

ሂደት ላይ፣ እርስ-በርስ የሚጋጩ ጥቅሞች ካጋጠሙና የግድ አንዱ መመረጥ ያለበት ከሆነ፣ የጥቅሞቹ መሠረታዊነት እና በሸሪዓ አንገብጋቢ ተብለው ከተለዩ ጥቅሞች ጋር ያላቸው ቀረቤታ፣ እና በግልጽ የሸሪዓ አስረጂዎችና መርሆዎች ያላቸው ድጋፍ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ የሚወሰን ይሆናል።[42]

ባጠቃላይ ሸሪዓ የሰውን ዓለማዊ ጥቅም *(መስላሃሕ)* የማስከበር ጠቅላላ ዓላማ ያነገበ የሕግ ሥርዓት ሲሆን፣ በተጓዳኝ በማንኛውም ማህበራዊ መስክ ብልሹነትን *(መፍሰዳሕ)* መከላከል በራሱ ጠቀሜታን የማስገኘትና የማስከበር አንድ አካል ነው። ከ*መስላሃሕ* መርሆዎች ላይ ሌሎች የሕግ ቀኖናዎች *(ቀዋዒድ አል-ፊቅሒያሕ)* የተቀሰሙ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል ‹ጥቅምን ከማስከበር በላይ በቅድሚያ ጉዳትን መከላከል›፣ እንዲሁም ‹ሁለንተናዊ ጉዳትን ለመከላከል ሲባል አንድ ልዩ ጉዳት እንዲደርስ መተው› የመሳሰሉ ጠቅላላ ተቀባይነት ያገኙ የሸሪዓ የሕግ ብሂሎች በመሆን ለሚነሱ አዳዲስ የሕግ ጭብጦች ሙሉ *ኢጅቲሓድ* ማድረግ ሳያስፈልግ፣ ቀጥተኛ መፍትሔ ለመስጠት ዝግጁ የሆኑ የሸሪዓ ቀኖናዎች ሊቀረጹ ችለዋል፡ ፡[43]

## 3. *መቃሲድን መለየት*

*መቃሲድን* ለመለየት የመጀመሪያው ዘዴ፣ የድንጋጌውን የሕግ ቅርጽ እና ቋንቋዊ መልዕክቱን በቀጥታ በመውሰድ፣ ዓላማውን መለየት ይቻላል። ክልካይ ሕግ ከሆነ መከልከሉ፣ አዛዥ ሕግ ከሆነ እንዲፈጸም ማዘዙ የሸሪዓው ዓላማ ነው በማለት *መቃሲድ* ከድንጋጌው ቋንቋዊ አገላለጽ ይወሰዳል። በሌላ አነጋገር፣ የድንጋጌው እማሬያዊ መልዕክት ከዓላማው ተለይቶ አይታይም። ይህን አቀራረብ እንደ ዟሒሪ ያሉ የቃል-በቃል የሕግ አረዳድ የሚከተሉ *መዝሓቦች* የሚከተሉት ሲሆን፣ የሸሪዓ ዓላማ ከሕጉ ድንጋጌ አገላለጽ ተለይቶ እንደማይታይ ያስረዳሉ።[44] ከድንጋጌው ቀጥተኛ መልዕክት በተጨማሪ፣ ከጀርባ ያለው የሕግ ምክንያት *(ዒላሕ)* ሊመረመር እና ሁለቱ የሕግ ገጽታዎች በአንድነት ሊታዩ ይገባል የሚለው፣ ኢማም አሽ-ሻጢቢን ጨምሮ የብዙኃኑ *ዑለማእ* የ*መቃሲድ* አቀራረብ ነው። ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ፣ የአንድ ድንጋጌ ትዕዛዝ ወይም ክልከላ በራሱ ድንጋጌው ሊያሳካው ያሳበው ወይም ከመነሻው የተደነገገበት ምክንያት ሊሆን አይችልም፤ ከትዕዛዝ ወይም ክልከላ ጀርባ ምንጊዜም አንድ ጥቅም የማስገኘት ወይም ጉዳትን የመከላከል ወይም ችግርን የመቅርፍ ግብ ይኖራል። ይህ የድንጋጌ ምክንያት ከቋንቋዊ መልዕክቱ ጋር ተዳምሮ ለ*መቃሲድ* ምርምር መነሻ ሊደረግ ይገባል። የድንጋጌዉ *ዒላሕ* በግልጽ በአንቀጹ ውስጥ ባልተመለከተ ጊዜ፣ የሕጉ ዓላማ *(ሂክማሕ)* ሙሉ በሙሉ በአንቀጹ አገላለጽ እና በወቅቱ የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ይመሰረታል።[45]

---

[42] Ibid., p. 230

[43] Ibid. የሸሪዓ ሕግ ቀኖናዎች *(ቀዋዒድ አል-ፊቅሒያሕ)* ራሱን የቻለ ሰፊ ትንታኔ የሚያስፈልገው፣ ከኡሱል አል-ፊቅሕ ርዕሰ-ጥናቶች መካከል አንዱ ነው።

[44] Muhammad Hashim Kamali, Maqasid al-Shariah Made Simple, Occassional paper Series 13, The International Institute of Islamic Thought, 2008, pp. 12-13. Available at: https://www.academia.edu/attachments/33761430/download_file?st=MTU0MTg2NTI2NCwyMTMuNTUuODMuMTI0LDY1MjE0NjM%3D&s=swp-toolbar&ct=MTU0MTg2NTI2MSwxNTQxODY1MjkyLDY1MjE0NjM= (Accessed: 10-Nov-18).

[45] Ibid., p. 13.

እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት፣ *ዒላሕ* ሲባል አንድ ልዩ የሸሪዓ ሕግ የተደነገገበትን የጀርባ ምክንያት ሲጠቁም፣ *ሂክማሕ* ደግሞ ድንጋጌው ሊያሳካዉ ያሰበውን ዓላማ ያመለክታል፡፡ ይህ ልዩ የድንጋጌ ዓላማ *(ሂክማሕ)* አጠቃላይ የሸሪዓ ዓላማ የሆነውን ጥቅምን ማስገኘት *(መስላሃሕ)* እና ጉዳትን ወይም ብልሹነትን መከላከልና ማስወገድ *(መፍሰዳሕ)* የሚያሳካ ንዑስ-ዓላማ ነው፡፡ በምሳሌ ግልጽ ለማድረግ ያህል፣ *ኸምር* (ወይን) የተከለከለበት ምክንያት *(ዒላሕ)* በአንቀጹ ያልተገለጸ በመሆኑ፣ *ኸምር* ለምን ተከለከለ በሚል ጥያቄ የአንቀጹን አገላለጽ እና የወቅቱን የቋንቋ አጠቃቀም መሠረት በማድረግ፣ የድንጋጌውን ምክንያት *(ዒላሕ)* መለየት የመጀመሪያው የ*ሙጅተሒድ* ተግባር ነው፡፡ *ኸምር* የተከለከለው አስካሪ በመሆኑ ምክንያት ከሆነ፣ ይህ የድንጋጌው *ዒላሕ* ይሆንና፣ አስካሪነቱ የተወገዘበት ጠቅላላ ምክንያትና ዓላማ ደግሞ የሰውን የአዕምሮ ሚዛን የሚያዛባና ጉዳት እንዲደርስ ስለሚያደርግ *መፍሰዳን* የመከላከል ዓላማ *(ሂክማሕ)* አለው ማለት ነው፡፡ በጥቅሉ፣ ጉዳትን መከላከል በራሱ ጥቅም የማስገኘት አካል በመሆኑ የጠቅላላው የሸሪዓ ሕግ ማዕቀፍ ዓላማ *መስላሃሕ* ነው ቢባል ስህተት የለውም፡፡ ከሕጉ አንቀጽ አገላለጽ እና የቃላት ፍች አኳያ የድንጋጌውን *ዒላሕ* መለየት አንቀጽን መሠረት ያደረገ ንድፈ-ሐሳባዊ *(የኡሱል)* አቀራረብ ሲሆን፣ የድንጋጌውን ዓላማ *(ሂክማሕ)* መለየት ደግሞ የ*መቃሲድ* (ተጨባጭ ዓላማን መሠረተ ያደረገ) አተያይ ነው፡፡[46] *መቃሲድን* መለየት የድንጋጌን ምክንያት *(ዒላሕ)* እንደመለየት ከባድ አይደለም፤ በተለይ *ዒላሕ* በሕጉ አንቀጽ ወይም ዘገባ በግልጽ ያልተመለከተ ከሆነ፣ የዐረፍተ-ነገሩን እማሬያዊ *(ሀቂቂ)* እና ፍካሬያዊ *(መጃዚ)* መልዕክት፣ ጥቅልነትና *(ዐም)* ዝርዝርነት *(ኻስ)* ወዘተ.. ባህርያት መሠረት አድርጎ መተንተን አስፈላጊ ስለሚሆን ሙያዊ ችሎታን ይጠይቃል፡፡[47]

*መቃሲድን* መለየት፣ ከሕጉ ቋንቋዊ ይዘት በዘለለ፣ ሰፋ ያለ አመክንዮኣዊ ምርምር የሚጠይቅ ነው፤ በዚህ ረገድ ከድንጋጌው አንቀጽ እና *ዒላሕ* በተጨማሪ፣ ሕጉ የወረደበት መንስኤ እና ከባቢያዊ እውነታ (አውድ) *(አስባብ አን-ኑዙል)* ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ሕግን ከወረደበት ወይም ከተደነገገበት ልዩ ምክንያት እና አጃቢ እውነታዎች ውጪ ቋንቋዊ (እማሬያዊ) መልዕክቱን ብቻ መከተል፣ ከሕጉ ዓላማና መንፈስ ውጪ ለተሳሳተ አረዳድና አተረጓጎም የሚዳርግ የመሆኑን ያህል፣ የ*አስባብ አን-ኑዙል* በቂ ግንዛቤ ደግሞ የሕግ አውጪዉን ዓላማ በትክክል ለመረዳት ወሳኝ ግብዓት መሆኑን፣ በቀደመው *የኡሱል አል-ፊቅሕ* እድገት የቃል በቃል የሕግ አረዳድ እና ከምንጮች ጋር በጥብቅ በተሳሰረ *ኢጅቲሓድ (ቂያስ* - ምስስሏዊ አመክንዮ) ላይ ተወስኖ የቆየ በመሆኑ፣ ለ*አስባብ አን-ኑዙል* ይሰጠው የነበረው ትኩረት አናሳ ነበር፤ በውጤቱም *መቃሲድ* የሚጠበቅበትን ያህል ታሪካዊ የ*ኡሱል* አሻራ እንዳይኖረው ሆኗል፡፡[48]

*መቃሲድ* ወደሚለይበት ዘዴ ስንመጣ፣ ብዙዎቹ የሸሪዓ መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን በማጥናት ዓላማቸውን መለየት አስቸጋሪ እንዳልሆነ አሽ-ሻጢቢ ይገልጻሉ፡፡ የሕጎቹን ዓላማዎች የሚያሟሉና የሚደግፉ ሌሎች ተጓዳኝ ዓላማዎችም ቢሆኑ የ*መቃሲድ* አካል ናቸው፡፡ ከቁርአንና የሕግ አንቀጾችና የሱናሕ የሕግ ዘገባዎች የተላለፉ ግልጽና ልዩ *(ቀጥዒ)*

---

[46] Kamali, Sharia Law, *supra* note 10, p. 128.

[47] Ibid., p.128 & 131.

[48] Ibid., pp. 130 &124.

ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ *መቃሲድን* መለየት አንዱ ዘዴ ነው፡፡[49] አሚይና ደጋፊ *(ሃጂያት)* ዓላማዎችን በተመለከተ፣ ለምሳሌ፡- በሕግ ግዴታ የተደረገን ተግባር *(ዋጂብ)* ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ፣ የግዴታነት ቅርጽ አላቸውን? ወይም እንዲሁም በሕግ ከተከለከለ ነገር ለመቆጠብ አስፈላጊ የሆነ ሁሉ፣ በክልከላው ዓላማ ውስጥ ይካተታልን? ለሚሉት ጥያቄዎች በጥቂት ዝርዝር ነጥቦች ላይ የምሁራን ልዩነት ቢንጸባረቅም፣ ከሕግ ትዕዛዝ ወይም ክልከላ ጀርባ ያሉ አስፈላጊ ነገሮች (ቅድመ-ሁኔታዎች) ሁሉ በትዕዛዙ (*ዋጂብ)* ወይም ክልከላው *(ሀራም)* ዓላማ ስር የሚወድቅ መሆኑ ላይ ጠቅላላ ስምምነት አለ፡፡[50]

*ለመቃሲድ* መንደርደያ የተደረገው የሸሪዓ አስረጂ ግልጽ ካልሆነ፣ ወይም *ዞኒ* (አሻሚ) ከሆነ፣ ጥቅል እና ግልጽ ካልሆኑ የሕግ አስረጂዎች ላይ *መቃሲድ* ከሚለይባቸው ወሳኝ ዘዴዎች መካከል አንዱ *ኢስቲቅራእ* (ዳሰሳዊ አረዳድ/*Induction)* ነው፡፡ አንድ ወይም ሁለት አንቀጾች ለየብቻቸው ግልጽ ባይሆኑም ሁሉም በአንድነት ሲነበቡ፣ ተነጣጥለው *ዞኒ* የነበሩት በሕብረት ግልጽ የሆነ መልዕክት የሚያስተላልፉበት እድል ሰፊ ነው፤ በዚህ ጊዜም ከእነዚህ በአንድ አጀንዳ ላይ ከሚያጠነጥኑ ድንጋጌዎች ላይ *መቃሲድ* በ*ኢስቲቅራእ* (በአንድነት በማንበብ) ሊለይ ይችላል፡፡ የልዩ ልዩ የሕግ ክፍሎችና ድንጋጌዎች ዓላማ ብቻ ሳይሆን በራሱ በ*መቃሲድ* ጥናት ዉስጥ *መሠረታዊ* የሆኑ፣ ለምሳሌ፣ ከታች እንደተብራራው፣ *መቃሲድ ዶሩሪ፣ ሃጂ፣ ተህሲኒ* በተሰኙ ሦስት ምድቦች *መመደቡ*፣ በ*ዶሩሪ መቃሲድ* ስር አምስቱ ማለትም እምነት፣ ሕይወት፣ እዕምሮ፣ ንብረት እና ትውልድ የሚካተቱ *መሆኑ*፣ በዚሁ በምሁራን ጥልቅ እና ጥቅል የቁርአንና የ*ሱናሕ* ጥናት *(ኢስቲቅራዕ)* ድምዳሜ ነው፡፡ ባጠቃላይ ሻጢቢ እንደሚያረጋግጡት አጠቃሏዊ አመክንዮ *(Inductive Reasoning) መቃሲድን* በመለየት ሂደት ዉስጥ ቀዳሚውን ሚና የሚጫወት ዘዴ ነው፡፡[51]

የሕጎችን ዓላማ በመለየትና አተረጓጎማቸውን እና ትግበራቸዉ ዓላማውን የተከተለ እንዲሆን ለማድረግ፣ እንዲሁም የተለዩት ዓላማዎችን ተንተርሶ በአዲስ ጭብጦች ላይ አዲስ ድንጋጌዎችን ለመቅረጽ እና ውሳኔዎችን ለመስጠት ይቻል ዘንድ በመጀመሪያ የተለየው *መቃሲድ* ከግላዊ ፍላጎት ወይም ቡድናዊ እሳቤ በራቀ አኳኋን መከናወኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ እንዲሁም ነገሩ ጥልቅ የምንጮችን ግንዘቤ የሚጠይቅ እንደመሆኑ፣ በዚህ ረገድ ሊፈጠር የሚችለውን ስህተት ለማስወገድና በቅንነት ይፈጸም ዘንድ፣ *በሙጅተሒዶች* በተናጠል ከሚከናወን ይልቅ፣ በጋር የሊቃውንት ምክክር የሚከናወንበት የሕብረት *ኢጅቲሓድ* ተቋማዊ አደረጃጀት (ምክር-ቤታዊ *ኢጅቲሓድ)* ሊፈጠር እንደሚገባና በዘመናዊ የሕግና ፖሊሲ አወጣጥ ሥርዓት ውስጥ ምሁራዊ አመራርና እገዛ የሚያደርግበት መዋቅር ሊዘረጋ እንደሚገባ ከማሊ ያስረዳሉ፡፡[52]

---

[49] Ibid., pp. 131-32.

[50] Ibid., p. 133.

[51] Ibid., pp. 132-133.

[52] Ibid., p. 136. *ኢጅቲሓድ በምሁራን ምክክር ወይም በዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር ውስጥ በሕዝብ በተቋቋመ የሕግ አዉጪ አካል (ፓርላማ) ውስጥ የሸሪዓ ሊቃዉንትን ባቀፈ የሸሪዓ ኮሚቴ አማካይነት የሚተገበርበት ተቋማዊ ቅርጽ አጥጋቢ በሆነ ደረጃ ያላደገ በመሆኑ አሁንም ቢሆን መቃሲድ ኢጅቲሓድን በማቃናት፣ እንዲሁም መቃሲድ የሕግ ዓላማዎችን ከማስጠበቅ በተቃራኒ ቅንነት ለጎደለዉ የግል ራዕይ ተገዥ እንዳይሆን በኢጅማዕ የሚፈጸምበት እድገት ገና የሚቀረው መሆኑን ምሁራን ያስረዳሉ፡፡* (ከማሊ፣ ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 170 -171 ይመለከቷል፡፡)

## 4. *መቃሲድ* እና *ኢጅቲሓድ*፡- *ኡሱልን - መቃሲድን መሠረት ያደረገ ኢጅቲሓድ*

*ኡሱልን መሠረት ያደረገው ኢጅቲሓድ* በዋናነት የቃል በቃል አረዳድ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ፣ እና ከዚህም አለፈ ከተባለ ከምስስላዊ አመክንዮ *(ቂያስ)* ስለማይዘል የቁርኣናዊ ሕጎችን የድንጋጌ ምክንያት *(ዒላሕ)* አሳማኝ በሆነ ደረጃ ለማስረዳት አይችልም፡፡ ለምሳሌ፡- ለሥርቆት ወንጀል የተቀመጠው ቅጣት እጅ መቁረጥ ነው፤ በ*ኡሱላዊ ኢጅቲሓድ* መሠረት የዚህ ድንጋጌ ምክንያት ምናልባት ሥርቆት በእጅ ስለሚፈጸም ነው ከማለት አያልፍም፡፡ *መቃሲድን* መሠረት ባደረገ የሕግ ምርምር ከሆነ ግን ሕጉ በወጣበት ጊዜ የነበረውን አካባቢያዊ ሁኔታ *(አስባብ አን-ኑዙል)* ይፈትሻል፤ እጅ መቁረጥ እንደ ቅጣት የተመረጠበትን ምክንያት ከወቅቱ፣ ከቦታው እና ከአካባቢያዊ ሁኔታው ጋር በማዛመድ ትንታኔ ይደረጋል፡፡ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ በያዝነዉ ምሳሌ እንግፋበት፤ የሚከተሉት ለሥርቆት ወንጀል ከተደነገገዉ የእጅ መቆረጥ ቅጣት ጀርባ ተከታዮቹ አጃቢ ሁኔታዎች በወቅቱ የአረቢያ ማሕበረሰብ መገለጫዎች ነበሩ፤ አንደኛ፣ ከኢስላም መምጣት በፊት ለሥርቆት እጅ መቁረጥ በአረቦች ይተገበር ነበር፤ ሁለተኛ፣ የወቅቱ የአረቢያ ማህበረሰብ ዘላን የነበረ በመሆኑ፣ ግጦሽ እና ውሃ ፍለጋ ግመሎቻቸውንና ድንኳናቸውን (ቤታቸውን) ይዘው የሚዞሩ ስለነበር የእሥራት ቅጣትን ማስፈጸም አይቻልም ነበር፤ ምክንያቱም የእስር ቅጣትን ለማስፈጸም ቋሚ እስር-ቤቶችን ማቋቋም እና ዋርዲያዎችን ማደራጀት፣ እንዲሁም ለእስረኞች መደበኛ የምግብ አቅርቦትና ሌሎች አገልግሎቶችን የያዘ የማረሚያ ቤት ተቋም ያስፈልጋል፡፡ አርብቶ-አደር እና ዘላን በሆነው የወቅቱ ማሕበረሰብ የንብረት መብትን ማስከበር እጅግ አንገብጋቢ ከመሆኑ ጋር፣ እንዲሁም ኢስላም በመጣበት ጊዜ የልማድና የአኗኗር ለውጥ ያልነበረ በመሆኑ ቀድሞ እንደነበረው የአረብ ልማዳዊ ሕግ ሁሉ የሸሪዓ ሕጉ ተመሳሳይ ቅጣት እንዲጸና አድርጓል፡፡[53] ተመሳሳይ አይነት ትንታኔ ለአመንዝራነት እና የወንጀሉን የማስረጃ አቀራረብ በተመለከተ ለተቀመጡት ቅድመ-ሁኔታዎች፣ እንዲሁም ሌሎች ቁርኣናዊ የወንጀል ቅጣቶች ላይ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በተለይም፣ ለአመንዝራነት የወንጀል ክስ፣ አራት የዐይን ምስክሮች እንዲቀርቡ የተደነገገው ከወቅቱ የምድረ-በዳ ላይ ሕይወት እና ዘላንነት ጋር ተያይዞ ተፋጻሚ ሊደረግ የሚችል ነበር፡፡ እዚህ ላይ አንገብጋቢ ጥያቄ የሚሆነው፣ በገጠርና በከተሞች ዉስጥ በአንድነት ሰፍሮና ተደላድሎ ለሚኖረው የዘመኑ ማሕበረሰብ እነዚህና መሰል የሸሪዓ ሕጎች አግባብነት አላቸውን? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ዘመን የሥልጣኔ ደረጃ፣ የሕብረተሰብ አደረጃጀት እና የግለሰብ አኗኗር አኳያ፣ የሴሰኝነት ወይም አመንዝራነት ወንጀል በአራት የዐይን ምስክሮች ይረጋገጥ ከተባለ ፍጹም የማይቻል ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ በ*ኡሱል* ላይ በተመረኮዘ *ኢጅቲሓድ* ከሆነ፣ እነዚህ እና መሰል የሸሪዓ ሕጎች የተደነገጉበትን አካባቢያዊ ሁኔታና ተጨባጭ እዉነታ ታሳቢ ሳይደረግ ሕጉ ቃል በቃል በቦታ እና በሁኔታ ሳይወሰን እንዲፈጸም ለማድረግ የሚሞክርና በመጨረሻም ተቀባይት እንዲያጣና በወረቀት ላይ ብቻ እንዲቀር የሚያደርግ ነው፡፡ ከጥንት ከሻፊዒ ጊዜ ጀምሮ፣ *ኢጅቲሓድ* በድንጋጌው አገላለጽ፣ ቃላት እና ሐረጋት ላይ ብቻ ታስሮ በ*ቂያስ* አማካይነት የሚደረግ ዉስን የምርምር ሂደት የነበረ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜም ለሕጉ መውጣት ምክንያት የሆነውን ዓላማ *(ሂክማሕ)* በሚያደናቅፍ አኳኋን ሲከናወን ቆይቷል፡፡ እንደ ሻጢቢ እና ሌሎች የ*መቃሲድ* ምሁራን እይታ ደግሞ ከሕግ የቃል በቃል ትርጓሜ ወይ *ቂያሳዊ* ድምዳሜ የሕጉን ዓላማ ያላነገበ፣ ደረቅ የቃላት ጨዋታ መሆን የለበትም፡፡[54] *አስባብ አን-*

[53] Ibid., pp. 130-131.

[54] Ibid., p. 127.

*ኑዙልን* ግምት ውስጥ በማስገባት እና የሸሪዓው ዓላማ ሳይሰናከል፣ ተጨባጩን እና ማህበረሰባዊ ለውጡን ያገናዘቡ ሌሎች አማራጭ ድንጋጌዎችን በመዘርጋት ሕጉ ያነገበውን ፍትሕንና መረጋጋትን የማስፈን ዓላማ *(መሷሊሕ)* እንዲያሳካ ማድረግ የሚቻለው *መቃሲድን መሠረት* ባደረገ *ኢጅቲሓድ* አማካይነት ነው፡፡[55]

*መቃሲድን መሠረት ያደረገ ኢጅቲሓድ* ደግሞ ለሕጉ መደንገግ የቅርብ ምክንያት ከሆነው *ዒላሕ* ባሻገር ሕጉ በመደንገጉ ለማሳካት በታሰበዉ ዓላማ ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ የሕግ ምርምር የሕጉን አገላለጽ መነሻ ያደረገ የሐሳብ መስመር *(ቂያስ)* የተከተለ ሳይሆን ጠቅላላ የሸሪዓ ዓላማ የሆነውን *የመስላሃን* ግብ እውን ለማድረግ ከሕጉ ጀርባ ያለውን ጥበብ፣ ምክንያተ-ድንጋጌ *(ሂክማሕ)* መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ ስለዚህ *የኡሱል ኢጅቲሓድ* እና *የመቃሲድ ኢጅቲሓድ* ሁለት የተለያየ አተያይ ያላቸው የሸሪዓ ምርምር አቀራረቦች መሆናቸውን ይገነዘቧል፡፡[56]

የ20ኛው ክፍለ-ዘመን *የመቃሲድ* ሊቃውንት መካከል ቀዳሚው የሆኑት ጧሒር ኢብን ዐሹር፣ *መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ አል-ኢስላሚያሕ* በተሰኘዉ ፋና-ወጊ መጽሃፋቸው እንደሚያስረዱት፣ የሸሪዓ *መቃሲድን* ያልተከተለ *ኢጅቲሓድ* ለስህተት እንደሚዳርግና፣ የሕጉን ዓላማና መንፈስ ወደ ጎን በመተዉ የግል እይታ በ*ኑሱስ* ጥቅሶች ውስጥ ጎልተዉ እንዲታዩ በማድረግ የአረዳድ ችግር ይፈጥራል፤ እንዲሁም *የመቃሲድ* እዉቀት *ኢጅቲሓድ* ለማድረግ *(ሙጅቲሒድ* ለመሆን) አንዱና ወሳኝ ቅድመ-ሁኔታ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ በሌላ በኩል፣ የሕጉን ቃላት ብቻ በመከተል የሚደረግ አተረጓጎም የሕጉ ዓላማ በሌላ ተጨባጩን በተከተለ አተረጓጎም ሊሳካ ቢችልም አላስፈላጊ የቃላት አክራሪነትን ያስከትላል፡፡ በምሳሌ ግልጽ ለማድርግ ያህል፣ የ*ዘካሕ* ወይም የ*ዘካሕ አል-ፊጥር* (በረመዳን ፆም መጨረሻ ለድሆች የሚሰጥ ምጽዋት) አከፋፋልን በተመለከተ በ*ሀዲስ* የተገለጸው በአይነት እንደሚከፈል ነው፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ አሽ-ሻፊዒ *ዘካሕ* በጥሬ ገንዘብ ሊከፈል አይችልም የሚል አቋም አላቸዉ፡፡ *ሀነፊዎች* ደግሞ የ*ዘካሕ* ዓላማ የድሆችን ፍላጎት ማሟላት እስከሆነ ድረስ በጥሬ ገንዘብ ቢሰጥ ዓላማዉ የማይደናቀፍ በመሆኑ በጥሬ ገንዘብ መክፈል ይፈቀዳል የሚል እይታ አላቸዉ፡፡[57] በአይነቱ እንዲከፈል የሚገልጹት *ሀዲሶች* የወቅቱን የአረቢያ ማህበረሰብ አኗኗር መሠረት በማድረግ የተላለፉ ናቸዉ፤ ስለሆነም ዓላማቸውን በመከተል ባለንበት ዘመን ማንኛዉም ንብረት በወረቀት ገንዘብ በሚወከልበትና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎትን ማሟላት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ *ዘካሕ* በገንዘብ ቢከፈል ከሕጉ ጋር የማይጻረር፣ ብሎም ዓላማውን ሙሉ በሙሉ እውን የሚያደርግ በመሆኑ የሻፊዒ *መዝሀብ* አቋም *መቃሲድን* ያላገናዘበ ነው ማለት ይቻላል፡፡[58]

በተጨማሪ ምሳሌ ለማብራራት፣ እንደ ኢማም ማሊክ እይታ *ዘካሕ* በዓመቱ መጨረሻ ከሚከፈልበት ጊዜ ቀደም ብሎ መክፍል የሚቻል መሆኑን ተጠይቀው፣ ከ*ሶላሕ* (ስግደት) ጋር በማመሳሰል (*ቂያስ* በማድረግ) *ሶላሕ* ከወቅቱ ውጪ እንደማይፈጸም ሁሉ *ዘካሕም* እንደዚሁ በወቅቱ ብቻ መከፈል ይኖርበታል የሚል *ፈትዋ* (ብይን) ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን

---

[55] Ibid., p. 131.

[56] Ibid., p. 128.

[57] Ibid., p. 137.

[58] Ibid.

እንደ ኢብን ዓረቢ (1148 አ.) እና ኢብን ሩሽድ (1126 አ.) ያሉ የእርሳቸው *መዝሓብ* ተከታይ ሊቃዉንት የማሊክ አቋም ቀልብሰው ከሕጉ ዓላማ አኳያ ለከፋዩ አመቺ እስከሆነ ድረስ *ዘካሕ* ቀድሞ ቢከፈል የማይከለከል ወይም የሚፈቀድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከዓላማ አንጻር ብቻ ሳይሆን *ዘካሕ* ከ*ሶላሕ* ጋር በተመሳሳይነት የታየበት አመክንዮ *(ቂያስ)* በራሱ ትክክል አይደለም፤ ምክንያቱም *ሶላሕ* የሚፈጸምበት ልዩ ጊዜ ተለይቶ የተደነገገ ሲሆን፣ ለ*ዘካሕ* አከፋፈል ደግሞ ልዩ ጊዜ ያልተቀመጠ በመሆኑ፣ *ዘካሕ* ቀደም ብሎ ለመክፈል የተፈቀደ መሆኑን አስረድተዋል፡፡[59]

ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* እና ብይኖች *(ፈታዋ)* የሚያስከትሉት ውጤት *(መዓላት)* ከወዲሁ ታሳቢ በማድረግ፣ ከሕጉ ዓላማ አንጻር አስፈላጊውን ማስተካከያ ማድረግ የ*መቃሲድ* አንዱ አካል ነው፡፡ ምንም እንኳ የሸሪዓ ምርምር የኢጅቲሓድ መርሆዎችንና *ሥነ-ሥርዓቱን* የጠበቀ ቢሆንም፣ የሚያስከትለው ውጤት የከፋ ከሆነና ሌላ የገዘፈ የሸሪዓ ዓላማ የሚያፈርስ ከሆነ ፍርዱ እንዳይፈጸም ወይም በርትዕ *(ኢስቲህሳን)* መሠረት በሌላ *መቃሲድን* ባገናዘበ አማራጭ ውሳኔ መተካት ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ፣ በቅድመ-ኢስላም የመካሕ አረቦች ካዕባን ሲገነቡ አብራሃም የካዕባን መሠረት ከጣለበት ትክክለኛ ቦታ ላይ ያልገነቡ መሆኑ እየታወቀ፣ ካዕባው ቀድሞ የተገነባበት ልዩ ቦታ ላይ እንደገና እንዲገነባ ከዓኢሻ በኩል ሐሳብ ቢቀርብም፣ ነቢዩ ሙሀመድ ግን እርምጃው በምዕመናን ላይ ሊያስከትለው የሚችለዉን የእምነት መዋዠቅ ችግር ታሳቢ በማድረግ፣ ካዕባው ባለበት እንዲቀጥል አድርገዋል፡፡[60] ከዚህ ዉሳኔ መረዳት የሚቻለዉ አንዳንዴ ሐቅን ለመከተል በሚደረገው ሙከራ ሌላ ታላቅ ዓላማ *(መቅሰድ)* የሚናድ ከሆነ ከውጤቱ አኳያ ዉሳኔው መልኩን እንዲቀይር ሊደረግ እንደሚገባና ሸሪዓም የሚደግፈው መሆኑን ነው፡፡[61]

---

[59] Ibid.

[60] Ibid.

[61] Ibid., p. 138.

*መቃሲድ* ከወንጀል ሕጎች አፈጻጸም አኳያ ሲታይ፣ አንድ የወንጀል ድንጋጌ እና ቅጣት የተደነገገበት ልዩ ምክንያት *(ዒላሕ)* እና ከባቢያዊ ሁኔታ *(አስባብ አን-ኑዙል)* ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ፣ የሕጉ ዓላማና መንፈስ ከተለየ በኋላ፣ ድንጋጌውን በአንድ በተለየ ጉዳይ ተፈጻሚ ሲደረግ፣ የወንጀል አድራጊውን፣ ድርጊቱን ያካበቡ ወሳኝ ፍሬ-ነገሮች ግምት ውስጥ ገብተው፣ እንደ ጉዳዩ ሁኔታ በርትዕ እሳቤ ላይ በተመረኮዘ የ*መቃሲድ* እሳቤ መሠረት ቅጣቱ ተፈጻሚ እንዳይሆን ሊታገድ ይችላል፡፡ ከወንጀል ፈጻሚዉ ግላዊ ሁኔታዎች በመነሳት ቅጣቱን ተፈጻሚ ከማድረግ ይልቅ፣ እንዳይፈጸም ማድረጉ የሕጉን ዓላማ የሚያሳካ ከሆነ፣ ከቃል በቃል የሕግ አረዳድ ይልቅ ለሕጉ ዓላማ ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ (kamali, Sharia law: an Introduction, *supra* note 10, pp. 138-139).

በሸሪዓ የወንጀል ሕግ እድገት፣ ከጠቅላላው የ*ኡሱል አል-ፊቅሕ* የሸሪዓ የፍትሐ-ብሔር እና የንግድ ሕግ ማዕቀፍ አንጻር፣ ገና በጅምር ላይ ያለ የሕግ ዘርፍ ነው፤ በቀደመው የ*ፊቅሕ ሥነ-ጽሁፍ* ውስጥ ጥቂት በቁርአንና በ*ሀዲስ* ተለይተው የተገለጹ የወንጀል ድንጋጌዎች ላይ ትንታኔዎችን የሚያቀርብ፣ እንዲሁም ከነቢዩ ሙሀመድ ባልደረቦች በኋላ በነበረው የተከታዮች *(ታቢዑን)* የከሊፋ *ሥርዓተ-መንግሥታት* እና የኢጅቲሓድ ዘመናት ላይ፣ በአንዳንድ የሸሪዓ የወንጀል ገጽታዎች ላይ *ኢጅቲሓድ* የተደረገ ቢሆንም፣ ከዚያ በኋላ፣ በተለይም የ*ኢጅቲሓድ* በር ተዘጋ ከተባለበት ከ11[ኛው] ክፍለ-ዘመን *መጀመሪያ* በኋላ በነበረው የ*ተቅሊድ* ባሕል መንሰራፋት፣ በተጓዳኝ የዓለም ሙስሊም ማህበረሰብ በጊዜ ሂደት ዘርፈ-ብዙ ለውጦችን ያስተናገደ ቢሆንም፣ የ*ተቅሊድን* ባህል ሰብሮ፣ የዘመኑን ማሕበረሰብ ተጨባጭ *መሠረት ያደረገ ኢጀቲሓዳዊ* የወንጀል ሕግ ምርምር ሲደረግ በስፋት አይስተዋልም፤ ከጥቂት ወራት በፊት፣ የዘመኑ የሸሪዓ ሊቅ የሆኑት ፕ/ር ሐሺም ከማሊ, በሸሪዓ የወንጀል ሕግ *(ሁዱድ)* ዙሪያ ከሚያጠነጥኑ ጥቂት አጫጭር የምርምር ጽሁፎቻቸዉ በተጨማሪ፣ ‹Islamic Criminal Law: Issues and Reform Proposals› የተሰኘ *ሥራቸውን* ለሕትመት እንደሰጡ፣ እና በዚህ *ሥራ* በርካታ የማሻሻያ እና የለውጥ ሐሳቦችን ያፈለቁ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፣ ወደፊት *ሁዱድ* የሚያድገበትን ትልም የሚያሳይ ፋና-ወጊ *ሥራ* ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ (see: IAIS Bulletin No. 39 July-August 2017, p. 10, Avaialable at: https://www.iais.org.my/e/attach/bulletin/2017/bulletin39.pdf (Accessed: 10-Nov-18).

ባጠቃላይ፣ *መቃሲድ* በሁለት መንገድ የ*ኢጅቲሓድ* መሪ ሊሆን ይችላል፤ አንደኛ ቀድሞ በሸሪዓ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ ዝርዝር ሕጎች ከተደነገጉበት ዓላማ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተፈጻሚ እንዲደረጉ በማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ቀድመው ከነበሩ ሕጎች ላይ በ*ኢስቲቅራእ* ከተለዩ የሸሪዓ ዓላማዎች ላይ በመነሳት ሌሎች አዲስ ሕጎች የሚቀረጹበትን ማዕቀፍ ይዘረጋል፤ በመሆኑም በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት አዲስ የሕግ ድንጋጌ *(ሁክም)* ላይ ለመድረስ ለሚደረገው ምርምር መንደርደሪያ መርሆ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 5. የ*መቃሲድ* አተያዮች

*መቃሲድ* ከተለያዩ የእሳቤ አቅጣጫዎች አንጻር በልዩ ልዩ ክፍል *ሥር* ሊመደብ ይችላል፤ እነሱም፣ ግለሰባዊ ሕይወትን መሠረት በማድረግ የሸሪዓ ዓላማዎች ካላቸው የአስፈላጊነት ደረጃ አንጻር፣ *ዶሩሪያት* (መሠረታዊ ፍላጎቶች)፣ *ሀጂያት* (አስፈላጊዎች/አሚይ) እና *ተህሲኒያት (ቅንጦቶች/ታካዮች)* የተሰኙ ናቸው፡፡ እምነትን፣ አካልን፣ ሐብትን፣ አዕምሮን (*ሥነ*-ልቦናን) እና የዘር ትውልድን ለመጠበቅ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የሕልውና ጥያቄዎች ሁሉ በ*ዶሩሪያት ሥር* የሚወድቅ ሲሆን፣ ጥቂት ምሁራን ደግሞ ከአምስቱ መሠረታውያን በተጨማሪ ክብር *(ዒርድ)* በ*ዶሩሪያት* ስር አካተዋል፡፡[62] በ*ሀጂያት* ስር የሚካተቱት *መቃሲድ* ደግሞ፣ ለሰብዓዊ ሕይወት እጅግ ጠቃሚ የሆኑ፤ ነገር ግን በተለይ ከግለሰብ ሕይወት አንጻር ሲታዩ፣ የሞት ሽረት ያላይደሉ ፍላጎቶች ናቸዉ፡፡ ለምሳሌ፡- ጋብቻ፣ ንግድ፣ መጓጓዣ ወዘተ.. የ*ሀጂያት* ዓላማዎች ከግል ሕይወት አንጻር ቢሟሉ ሕይወትን ምቹና ደስተኛ እንዲሆን የሚያደርጉ ቢሆንም፣ ሳይሟሉ ቢቀር፣ ሕይወትን አደጋ ላይ የሚጥሉ አይደሉም፡፡ ከግል ሕይወት ባለፈ፣ በማህበረሰብ ደረጃ የማይሟሉበት ሁኔታ የተንሰራፋ ከሆነ፣ ከአስፈላጊነት ወደ አስገዳጅ *(ዶሩሪያት)* ዓላማዎች ይሸጋገራሉ፡፡ በሦስተኛ ደረጃ፣ የ*ሥነ*-ዉበት እና ቅንጦት ባህሪ ያላቸዉ ዓላማዎች ደግሞ በ*ተህሲኒያት* ስር ይወድቃሉ፤ ለምሳሌ፡- ያማረ አለባበስ፣ የተዋቡ መኖሪያ ቤቶች.. ወዘተ፡፡[63] በሦስቱ የዓላማ እርከኖች መካከል ተዛምዶና አንዱ ለሌላው ቅድመ-ሁኔታ የሚሆንበት ትስስር እንዳለ መረዳት ይቻላል፤ ነገር ግን የሸሪዓ ድንጋጌው ቀጥተኛ ዓላማ ምንድን ነው ከሚለው አንጻር፣ ዓላማዎች ለሰው ምድራዊ ሕልውናና ሕይወት ያላቸውን የአስፈላጊነት ደረጃ በመመዘን፣ ከላይ ባጭሩ በተገለጸው አኳኋን፣ ከሦስቱ በአንዱ *መቅሰድ ሥር* ሊመደቡ ይችላሉ፡፡[64] በሌላ አገላለጽ፣ የአንድ ድንጋጌ ዓላማ ምንድን ነው ሲባል፣ የጋብቻ ግንኙነትን መጠበቅ ነው ከተባለ፣ የ*ሃጂያት* ዓላማ አለው ማለት ነው፤ ነገር ግን የባለትዳሮችን የጋራ ንብረት መብት የሚያረጋግጥ ከሆነ፣ ተጋቢዎች እንደ ግለሰብ ያላቸውን የንብረት መብት የሚያስከብር በመሆኑ፣ ሕጉ *ዶሩሪ* ዓላማ ያዘለ ነው፡፡ በሦስቱ የ*መቃሲድ* መካከል ግጭት ቢያጋጥም፣

---

[62] በሸሪዓ ሊቃውንት ጥናት የተለዩት አምስት መለኮታዊ-ሰብዓዊ መሠረቶች አስፈልጎቶች፣ አብረሓም ማስሎው፣ እ.ኤ.አ በ1943 አምስት ተዋረዳዊ ሰብዓዊ ፍላጎቶች ብሎ የለያቸውና፣ በ1977 ደግሞ ሰባት ካደረሳቸው መሠረታዊ የሰው ፍላጎቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡ የያሲር ዐውዳ ‹Maqasid Al-Shariah፡ A Beginner's Guide, Occassional Papers Series 14, The International Institute of Islamic Thought (2008)› *ገጽ* 6 ይመለከቷል፡፡

[63] Jasser Auda, Maqasid Al-Shariah፡ A Beginner's Guide, Occassional Papers Series 14, The International Institute of Islamic Thought (2008), pp. 4-5. Available at: https://www.muslim-library.com/dl/books/English_Maqasid_alShariah_A_Beginners_Guide.pdf (Accessed: 10-Nov-18).

[64] Ibid., p. 5.

እንደ አስፈላጊነታቸው *ዶሩሪያሕ* ቅድሚያ ይሰጠውና፣ ከዚያም *ሀጂያት*፣ ከዚያም *ተህሲኒያት* ዓላማዎች ተመራጭ ይሆናሉ፡፡[65]

*መቃሲድ* ካለው የጽንሰ-ሐሳብና የተፈጻሚነት ወሰን አኳያ ደግሞ፣ *መቃሲድ* ጠቅላላ ዓላማዎች *(አል-መቃሲድ አል-ዐማሕ)* እና ንዑስ ዓላማዎች *(አል-መቃሲድ አል-ኻሷሕ)* ተብሎ በሁለት ክፍል ሊታይ ይችላል፡፡[66] በዚህ ረገድ፣ *መቃሲድ* ማለት በየደረጃው ለሚነሳው የ‹ለምን› ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ እንደመሆኑ፣ ከዚህ አንጻር ከአንድ ልዩ የድንጋጌ ምክንያት ጀምሮ፣ የሕጎች *መቃሲድ* ከልዩ *(ኻስ)* ዓላማ ወደ ጥቅል *(ዐም)* እያደገ እንደሚሄድ፣ ይህን ሐሳብ *መሠረት* በማድረግ፣ የ‹ለምን› ጥያቄ እና የሕጉ *መቃሲድ* ምንድን ነው የሚሉት ጥያቄዎች ተመሳሳይ እንደሆኑ፤ ጃሲር ዐዉዳ ያስረዳሉ፡፡[67] የአጠቃላይ የኢስላም እና የሸሪዓ ዓላማዎች የሚባሉት፣ ፍትሕ *(ዐድል)*፣ ‹ጉዳትን *(ዶረር)* መከላከል›፣ *መሠረታዊ* ሰብዓዊ *መ*ብቶችና አስፈልጎቶች *መሟ*ላት የ*መ*ሳሰሉት ጥቅል ዓላማዎች ለሁሉም የሸሪዓ ሕግ ንዑስ ዘርፍ አግባብነት ያላቸው እና የዓላማነት ሚናቸው በተወሰኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የማይገደብ ጠቅላይ እና ሁሉ-ገብ ዓላማዎች ናቸው፡፡[68] በሌላ በኩል ደግሞ፣ ለውስን የሕግ ዘርፎችና ግንኙነቶች ብቻ የተቀየሱ ንዑስ ዓላማዎች አሉ፤ እነዚህ ንዑስ ዓላማዎች የአንድን ልዩ የሕግ ዘርፍ አረዳድ እና አተረጓጎም መልክ እና አቅጣጫ የሚያስይዙ ሲሆን፣ የመጨረሻ ውጤታቸው ጠቅላላ የሸሪዓ ዓላማዎችን ከግብ የሚያደርሱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በቤተሰብ ጉዳዮች፣ የንግድ እና የገንዘብ ግንኙነቶችን፣ የአሠሪና ሰራተኛ ግንኙነት የሚገዙ ሕጎች፣ የወንጀል ሕግ፣ የ*ሥነ-ሥ*ርዓት ሕጎች ወዘተ.. አንዱ ከሌላው የሚለይበት የየራሳቸው ዓላማዎች አላቸው፡፡[69]

የቀደመው የ*መቃሲድ* ጥናት፣ ከግለሰብ ጥቅም አኳያ ከላይ በተጠቀሱት *ሦ*ስት የሸሪዓ ዓላማዎች ላይ የተገደበ ነበር፤ ይህን ውስን አተያይ በማስፋት እንደ ኢብን ዐሹር ያሉ ሊቃውንት፣ ማህበረሰብ፣ ሃገርን፣ ሕዝበ-ሙስሊሙን *(ኡማሕ)* እንዲሁም አጠቃላይ የሰዉ ዘርን የተመለከቱ የሸሪዓ ዓላማዎችን አስተዋውቀዋል፡፡ ይህ ማህበረሰብን *መሠረት* ያደረገ የ*መቃሲድ* አመዳደብ፣ በሃገር እና በዓለም-አቀፍ ደረጃ እየተነሱ ላሉ አዳዲስ ሸሪዓዊ ጭብጦች እልባት ለመስጠት መሪ በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡[70] ለምሳሌ፡- የ20ኛው ክፍለ-ዘመን የ*መቃሲድ* አጥኚ የሆኑት ረሺድ ሪዷ፣ ‹የሴቶችን መብትና ጥቅም ማስከበር› እና ‹ነባራዊ እውነታዎችን የተከተለ የሕግ ተሃድሶ› የሸሪዓ ዓላማዎች ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ፣ ዩሱፍ አል-ቀርዷዊ ደግሞ፣ ‹ሰው በሰውነቱ የሚጎናጸፋቸውን ክብሮችና መብቶች ማረጋገጥና ማስከበር› ሁለንተናዊ የሸሪዓ ዓላማ እንደሆነ በ*መቃሲድ* እሳቤያቸው ያስረዳሉ፡፡[71]

ሌላው *መቃሲድ* የሚመደብበት አተያይ፣ የተለየው ዓላማ የተ*መሠረ*ተበት አስረጅ ግልጽነት ላይ የተመረኮዘ ነው፤ በግልጽ የቁርአን ወይም የሱናሕ ማስረጃ *(ኑሱስ)* ላይ የተደገፉ የሸሪዓ

[65] Kamali, Sharia Law, *supra* note 10, p. 136.

[66] Ibid., p. 134.

[67] Jasser, *Maqasid Al-Shariah*፡ A Beginner's Guide, *supra* note 60, pp. 1-2.

[68] Ibid., p. 7.

[69] Kamali, Sharia Law, *supra* note 10, p. 134.

[70] Jasser, Maqasid al-Shariah፡ A Beginner's Guide, *supra* note 60, pp. 7-8.

[71] Ibid.

ዓላማዎች ‹*አል-መቃሲድ አል-ቀጥዒያሕ* (የተረጋገጡ ዓላማዎች)› ሲባሉ፣ አስረጂው ግልጽነት የጎደለው፣ አሻሚ ከሆነ ደግሞ ‹*አል-መቃሲድ አዝ-ዞኒያሕ* (አከራካሪ ዓላማዎች)› ይባላሉ፤ እነዚህ ዓላማዎች ተቃራኒ ወይም የተለየ መከራከሪያ ሊቀርብባቸው የሚችሉ፣ ለትርጉም የተጋለጡ ናቸው።[72] ወሳኝና አንገብጋቢ የሚባሉት የሸሪዓ ግቦች *(ዶሩሪያት)* በግልጽ አስረጂዎች የተረጋገጡ በመሆናቸው፣ ሁሉም *ዶሩሪያት* የተረጋገጡ *(ቀጥዒ) መቃሲድ* ናቸው ሊባሉ ይችላሉ፤ እንዲሁም ከ*ኑሱስ* አስረጂዎች ላይ በአጠቃላዊ ጥናት/አረዳድ *(ኢስቲቅራእ/Induction)* ወይም ከብዙ ግልጽ አስረጂዎች ላይ የተቀሰመ የ*መቃሲድ* ድምዳሜ እንደ *ቀጥዒ መቃሲድ* ሊወሰድ እንደሚችል ከማሊ ያስረዳሉ።[73] ከዚህ ውጪ አስረጂዉ ጥቅል ከሆነ ወይም ልዩ ቢሆንም አሻሚ የሆነ እንደሆነ፣ ከዚህ ድንጋጌ ላይ ተመርኩዞ የተለየ ዓላማ አሻሚ *መቃሲድ* ነው። በቤተ-ዘመዶች መካከል መረዳዳት ሊኖር ይገባል፤ ስለሆነም በሕግ በተወሰነ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የቀለብ ግዴታ ተወስኗል፤ በተጨማሪም የንብረት መብት እና የግለሰብ ክብር መጠበቅ ዓላማዎች፣ በግልጽ በሸሪዓ አስረጂዎች የተደገፉ በመሆኑ፣ ዓላማነታቸው አከራካሪ አይደለም።[74] በ*ቀጥዒ* እና አሻሚ *መቃሲድ* መካከል ግጭት ቢፈጠር፣ በግልጽ *(ነስ)* አስረጅ የተደገፈው *መቃሲድ* ተመራጭ እንደሚሆን ግልጽ ነው።[75]

የመስኩ ምሁራን ሌሎች የ*መቃሲድ* የአመዳደብ ዘዴዎችን ጨምረዋል፤ ከነዚህም መካከል፣ ተቀዳሚ ዓላማዎች *(አል-መቃሲድ አል-አስሊያሕ)* እና ተጓዳኝ ዓላማዎች *(አል-መቃሲድ አል-ተብዒያሕ)* አንዱ ነው፤ በዚህ አመዳደብ፣ በሕጉ ለማሳካት የታሰበው ዋነኛው ዓላማ ‹ተቀዳሚ *መቃሲድ*› ሲሆን፣ ከዚህ ዓላማ መሳካት በተጓዳኝ እውን እንዲሆን የታሰበው መለስተኛ ዓላማ ደግሞ ‹ተጓዳኝ *መቃሲድ*› ይባላል። የሕጉ አተረጓጎም *ሥልታዊ (ሂያል/legal Stratagems)* ሆኖ፣ ዋነኛ ግቡን ስቶ ተጓዳኝ ዓላማውን በማሳካት ላይ ያነጣጠረ መሆን የለበትም፤ የሕግ አረዳድ የዓላማዎቹን ተቀዳሚነት የተከተለ መሆን ይኖርበታል። ለምሳሌ፡- የእውቀትና የትምህርት ዋነኛ ዓላማ የ*ሥነ*-ፍጥረቱን አስገኚ እና የሕይወትን ዓላማ ማወቅ፣ እንዲሁም ምድራዊ ሕይወት ይህን ዓላማ የተከተለ እንዲሆን ለማድረግ ቢሆንም፣ እግረ-መንገዱን የብቃት ማረጋገጫ፣ የክብር ደረጃ ለማግኘት እና የገቢ ምንጭ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።[76]

## ማጠቃለያ

*መቃሲድን* ማወቅ፣ በተለይ የሸሪዓ ዓላማዎች በፊት ከነበረበት የግለሰባዊነት አዙሪት ወጥቶ በሁለንተናዊ ሰብዓዊ መብቶች፣ በተለይም የሴቶች መብት መከበር ከጠቅላላ ዓላማዎቹ መካከል አንዱ እንደሆነ አጽንኦት ባገኘበት በዚህ ክፍለ-ዘመን፣ በመስኩ ምሁራን ከግራም ከቀኝም የሚሰነዘሩ የ*መቃሲድ* ሐሳቦችን እና አዲስ እይታዎችን መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው። ሸሪዓን ከዘመናዊ የማህበረሰብ እውነታዎችና አስተሳሰቦች ጋር በማጣጣም ረገድ፣ ከሸሪዓ ማዕቀፍ ውጪ ባደገው የሰብዓዊ መብት አስተሳሰብ ለማረም ከመሞከር፣ ወይም

[72] Kamali, Sharia Law, *supra* note 10, p. 134.

[73] Ibid., p. 135.

[74] Kamali, Maqasid al-Shariah Made Simple, *supra* note 43, p. 7.

[75] Ibid.

[76] Kamali, Sharia Law, *supra* note 10, p. 135.

በሌላ አገላለጽ ሸሪዓን በውጫዊ የለውጥ ተጽእኖዎች ለመለወጥ ሙከራ ቢደረግ የተፈለገውን ዉጤት ማስመዝገብ አይቻልም፡፡[77] ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ለመዋሃድ እና ተቀባይነት ለማግኘት ሲባል የሸሪዓን ነባራዊነትና ተለማጭነት ማረጋገጥ አይቻልም፤ ስለሆነም ለውጡ እና ተሃድሶው ከዉስጥ የመጣ መሆን አለበት፤ ለዚህ አይነተኛዉ መሳሪያ ደግሞ በጥንታዊው የሉሉል እድገት ዉስጥ ተገቢውን ድርሻ ያላገኘውና የክፍለ-ዘመኑን *ዑለማእ* ትኩረት የሳበው *መቃሲድ* ነው፡፡ በሸሪዓ ሕግ ላይ የሚነሱ ዘመነኛ ንድፈ-ሐሳባዊና ተጨባጭ ጭብጦች እና ተግዳሮቶች፣ ከራሱ ከሸሪዓዉ በመነሳት ምንጩን ያለቀቀ መፍትሔ ሊሰጣቸዉ ይችላል፤ እንዴት ከተባለ የሸሪዓ ዓላማዎችን መሠረት ያደረጉ አዳዲስ ጥናቶችና እይታዎች *(ኢጅቲሓድ)* ሲዳብሩ ነው፡፡ ሸሪዓን ከዓለም-አቀፍ ሰብዓዊ መብት እሴቶችና የልማት ፖሊሲዎች ጋር እንዲጣጣምና የራሱ እሴቶች አድርጎ ይቀበላቸው ዘንድ፣ በተጀመረው የመቃሲድ የእውቀትና ሥነ-ጽሁፍ ጅማሮ ላይ ዓለም-አቀፋዊና አካባቢያዊ ተራማጅ ምልከታዎች ሊዳብሩ ይገባል፡፡[78]

ከኢትዮጵያ ሕግ ሥርዓት ጋር አግባብነት ባለዉ መልኩ፣ የ*መቃሲድ* ግንዛቤ የሸሪዓ የግልና የቤተሰብ ሕግ አተገባበር ማዕቀፉ በፌዴራል እና በክልል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተፈጻሚ እየተደረገ መሆኑን ተከትሎ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ሰብዓዊ መብቶች፣ በተለይም በቤተሰብ ግንኙነት ዉስጥ ጥሰት ሊፈጸምባቸው የሚችሉ የሴቶችና የሕጻናት መብቶችን ያከበረ እና የሚያስከብር የሕግ አተረጓጎም እንዲሰፍን ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ለክልልና ለፌዴራል የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እየቀረቡ ያሉ የቤተሰብና የውርስ ጉዳዮች፣ ከ*መዝሓብ* የቡድናዊነት አተረጓጎም ርቆ ከሸሪዓ ሕግ ዓላማዎች ጋር በተጣጣመ አኳኋን እንዲተረጎሙ በማድረግ ረገድ፣ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን በዘመኑ የሸሪዓ *መቃሲድ* እውቀት የማነጽ እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ዝርዝር የሸሪዓ ድንጋጌዎችን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ከሕጎቹ ጀረባ ያለው ዓላማ፣ እና ሸሪዓ በጠቅላላው ያነገበውን የፍትሕና የ*መሷሊሕ* ዓላማ ባገናዘበ መሆን ይገባዋል፡፡ በትምህርት መስክ፣ የ*መቃሲድ* ጥናት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የኢስላም ሕግ ጥናት አካል ሆኖ ይቀርብ ዘንድ፣ ነባሩን የሸሪዓ ትምህርት አቀራረብና የመማሪያ ሞዱል መሠረታዊ የይዘት እና የአቀራረብ ለውጥ ሊደረግበት ይገባል፤ በዚህ ረገድ የሕግ ትምህርትንና ጥናትን በማሻሻልና በማዘመን ረገድ ኃላፊነት የተጣለበት፣ የፍትሕና የሕግ ምርምር ኢንስቲቲዩት የሚጠበቅበትንም ሚና እንዲጫወት ይጠበቃል፡፡[79] ይህ ጽሁፍ የ*መቃሲድን* ምንነት፣ *መቃሲድ* የሚለይባቸውን ዘዴዎችና ጠቅላላ የሸሪዓ ዓላማዎችን ካስተዋወቀ ዘንድ፣ በኢትዮጵያ ተግባራዊ እየሆነ ያለው የሸሪዓ የቤተሰብ ሕግ ዓላማዎች ምንድን ናቸው? የሕጎቹ አተረጓጎምና አፈጻጸም በምን መልኩ ሊሆን ይገባል? የመሳሰሉ ጥያቄዎች፣ በተጨባጭ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አሰራር በመቃኘት፣ የሸሪዓን የቤተሰብ ሕግ ማዕቀፍ፣ *መቃሲድ* እና ተጨባጭ ችግሮችን በአንድነት መተንተን የሌላ ጥናት ርዕስ ይሆናል፡፡

---

[77] Jasser, Maqasid al-Shariah፡ A Beginner's Guide, *supra* note 60 pp. 22-23.

[78] Ibid, p. 23.

[79] የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 22/1990፣ አንቀጽ 5(7).

# Objectives of Sharia Law *(Maqasid Al-Shariah)*

*Alyu Abate Yimam*♣

## Abstract

*Pluralism is one of the essential features of the Ethiopian legal system. It is enunciated in the FDRE Constitution that religious and customary systems of dispute resolution are officially allowed to play their part on personal and family matters alongside the regular justice system. This pluralistic aspect of the Constitution has been officially reduced into reality by Sharia Courts of the Country that have been in operation since the time before Hailesilassie; and with the adoption of the FDRE Constitution, their parallel operation is guaranteed and made mandatory for recognition by the legislative organs of the country. Accordingly, Sharia courts have been restructured along federal structure and a three-tiered Sharia court levels are adopted both at the federal and regional levels. It is stated in the Federal Sharia Courts Consolidation Proclamation that Sharia courts shall apply Islamic law to adjudicate cases falling under their material jurisdiction (Art. 6). One of foundational concepts and currently reviving theme of Islamic jurisprudence is Maqasid Al-Sharia (the Purpose and Goals of Islamic Law). This work introduces the methodologies employed in identification of Maqasid, and the goals the Sharia aims to achieve through its diverse legal frameworks It is pointed out by the classical and contemporary Sharia literature and Maqasid jurists that different branches of Islamic law including its personal and family framework have objectives to realize which falls in either of one or more of the three cardinal goals i.e. Consideration of public interest (Maslahah), establishing Justice (Adl) and Educating an Individual (Tahdhib al-Fard). This paper presents an introductory analysis in the methodological exposition of Maqasid so as to tackle the difficulties arising from literalistic understanding of Sharia rules in general, and ensure correct and acceptable interpretation and enforcement of Islamic personal and family laws by the Ethiopian Sharia courts.*

**Key Words:** *Maqasid*, Objectives of *Shariah*, Juristic Reasoning *(Ijtihad*), Public Interest *(Maslahah),* Justice *(Adl)*

♣ LL.M, Addis Ababa University; LL.B, Haramaya University; Lecturer in Law, Wollo University. Email: alyuabate09@gmail.com.